# ፍጹም ነጻ መውጣት

ዛሬ ጠዋት ምን ማለት እንዳለብኝ አላውቅም ነበር። ከወንድም ኢጋን ጋር እዚያ ከኋላ ተቀምጬ፡ ወንድም ኔቪል የሆነ ነገር ሲናገር... እየሰማሁት፡ ወደ እኔ እየተመለከተ ነበር። እኔም ወንድም ኢጋንን "እየጠራኝ ነው እንዴ፡" አልኩት?

እርሱም፡ "አዎን እየጠራህ ነው" አለኝ።

2 ከዚያም ይሄው ዛሬ ጠዋት አንድ ነገር ለመናገር እዚህ መጥቻለሁ። ሳሰበው፡ እ... እዚያ ጋር ያለው የአየር ማቀዥቀዣ፡ ድ... ድምጹን ይጎትተዋል፡ ስትናገሩ፡ ድምጻችሁን ይዞ የሚሄድ ይመስላል። ድምጼ እንዳይሰማችሁ የሚያደርግ ይመስላል።

ለ... ለሴትየዋ በሰልክ ለመጸለይ እዚያ ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ ምስክርነት እየሰማሁ ነበር። ከዶክተር ሞሪሰን ሚስት፡ መልዕክቱን የተቀበለው ሰው፡ የሚደውልበትን ቦታና ከተማ ማስቀመጥ ረስቶ ነበር። እኔም ስለጸሎታችሁ፡ ለእኔም ጭምር፡ ስጸልይ ያደረግኩትን ልንገራችሁ። እጆቼን በሰልኩ ላይ ጭኜ፡ ቍጥሩ የትም ይሁን የት፡ ወደ ቁጥር እየጠቆምኩ፡ መንፈስ ቅዱስ ወደ ሴቲቱ እንዲሄድ ጠየቅኩት። ከዚህ በፊት እንደሚሰማ ሁሉ በተመሳሳይ መንገድ ይሰማዋል... አያችሁ? በቃ በእግዚአብሔር እጅ ተውኩት። ምናልባትም ጌታ የፈለገው በዚህ መንገድ ሊሆን ይችላል። አያችሁ? ምናልባትም እንደዚህ ቢሆን የተሻለ ሊሆን ይችላል።

3 ከዚያም እዚያ ሳለሁ አንድ ሰው ሲመሰክር ሰማሁ፡ ስለ እህት ሩክ አንድ ሰው የነገረኝ ነገር አለ... የአእምሮ ህመም እንዳመማት የ—የነገረኝ፡ ወንድም ኔቪል ይመስለኛል። አንድ ነገር በማስታወስ፡ በእግዚአብሔር እንደገፍ፡ እግዚአብሔር የእርሱ የሆኑትን ያውቃል። ስለእነሱ ሁሉንም ነገር ያውቃል።

4 ከኋላ ያላችሁ በደንብ ይሰማችኋል? ካልሆነ፡ እዚህ ጥቂት ባዶ መቀመጫዎች አሉ። ከፈለጋችሁ መቀየር ትችላላችሁ። እና፡ እስቲ እንየው፡ ዋናው ማይክሮፎን **ይህ** ነው? [አንድ ወንድም፡ "አይደለም፡ ጌታዬ" አለ።—አርታዒ።] ዋናው ማይክሮፎን **ይሄኛው** ነው? እሺ። ትንሽ አሰጠግተን የሚስተካከል ከሆነ እናያለን። እዚህ አከባቢ እንዴት ነው፡ ጂን? ያ ጥሩ ነው። አንዳንዴ ትንሽ ድምጼ ይሻክራል፣ ምክንያቱም ብዙ ጊዜ በተከታታይ ስለምሰብክ ነው። አሁንስ ይሻላል? አሁንስ በደንብ ይሰማችኋል?

5 ይህንንም በጸሎት እናስታውሳለን። ስለተከበረ ሰብሰባችን ማሳወቅ እንፈልጋለን...

እኅት ሩክን እያየኋት ነውን? ከኋላ በኩል እሷን የምትመስል ሴት ያየኋት መሰሎኝ ነው። "በእርግጠኝነት ሁለት የተለያዩ ነገሮች እያወራው አይደለም፡" ብዬ አስባለሁ። ከኋላ በኩል፡ እሷን የምትመስል ሴት እያየሁ ነው። በቅዱስ ኤድዋርድ ሆስፒታል ውስጥ ነች።

6 ስለዚህም፡ በክሊቭላንድ፡ ቴነሲ፡ እንዲሁም በካሊፎርኒያ፡ ግሩም ስብሰባዎችን አድርገናል። ጌታ እጅግ ባርኮናል፡ ብዙ ነገር አድርጓል። በዚህም

ደስተኞች ነን። ወደ ጉባኢያችን ተመልሰን፣ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ምሕረት በመናገራችን ደስተኞች ነን። ያኔም በመጽሐፍ ቅዱስ አካሄዳቸው ይህ ነበር።

7 የወንድም ኔቪል፣ ወይም የወንድም ቢለር ጸሎት እያደነቅሁት ነበር፣ ለሕዝቡ እርዳታና ምሕረትን እየጠየቀ፣ እንዴት እ—እንደጸለየ። ሁል ጊዜም፣ በጥንቃቄ ብንመለከተው፣ በሚሆኑ ነገሮች ሁሉ ላይ፣ እውነተኛ የሆነ ነገር ታያላችሁ። ከዚያም ወንድም ኔቪል መጥቶ እነዚህን ዲያቆናትና፣ የመሳሰሉትን፣ ወደዚህ መድረክ አምጥቷቸው፣ ቤተክርስቲያን ባቀረበችው ስ—ስጦታ ላይ የእግዚአብሔርን በረከት ሲ—ሲያውጅ ሰማሁት፣ ስለ እነዚያ ሰዎች፣ እንዴት እርስ በርሳቸው መጸለይ እንዳለባቸው፣ ለእግዚአብሔር ጸሎት ሲያደርግ ሰማሁት። ፓስተሩ ለዲያቆኖቹ ሲጸልይ፣ ዲያቆኖቹም መልሰው ለፓስተሩ ሲፀልዩ መስማት በጣም ያስደሰተኛል። እንግዲህ፣ አንድ ቤተክርስቲያን በዚህ መልኩ ስትተባበር ስትመለከቱ፣ የሆነ ነገር ሊሆን ነው ማለት ነው። ቤተክርስቲያኗ በሥርዓት መሆን ያለባት በዚህ መንገድ ነው። ይህም ለስብከቴ ሃሳብ ይሰጠኛል። የቃዴስ በረከትና የሰላዮቹን ሪፖርት አለመስማት፣ በሚል ርዕስ ለመናገር ፈልጌ ነበር፣ ነገር ግን በኋላ ሃሳቤን ቀይሬ፣ ሌላ ነገር አሰብኩ።

8 አሁንም፣ ፈውስ በተመለከተ፣ መናገር የምፈልገው አንድ ትንሽ ምስክርነት አለኝ። ልጄ፣ ቢሊን፣ ከኋላ ይኖራል ብዬ ተስፋ አድርጌ ነበር፣ ይሁን እንጂ ኪሱ ውስጥ ይዞታል።

እናም ቢሊ ከፊት ይልቅ፣ በጉባኤዎቹ ላይ እጅግ እየተሻሻለ ነው። ድሮ ይጨነቃል፣ ይበሳጫል፣ ሰዎቹን፣ "ኧረ፣ ተቀመጡ! ተቀመጡ!" "የጸሎት ካርድ እሰጣችኋለሁ፣" ይላቸው ነበር። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን፣ በስብሰባው ላይ ለሰዎች በጣም ሲራራላቸው፣ እስተውያለሁ። የቀረ የጸሎት ካርዶች ከሌለው፣ እንድጸልይላቸው ክፍል ውስጥ ያስቀምጣቸዋል።

9 እንደዚህ አይነት ነገር፣ በቺካጎ ባለፈው ሆኗል። ቢሊ ወደዚህ ከመጣ ያንን ደብዳቤ ማንበብ እፈልጋለሁ። እሱን በጭራሽ አላገኘሁትም። ዛሬ ጠዋት፣ ወደዚህ እንደምመጣና፣ ደ—ደብዳቤውን እ—እንደፈለግኩት አላወቀም። ስለ ብዙ በሽታ ሳስብ ግን ትዝ አለኝ። እንደዚህ ነው የሆነው። ይህ የምስክር ወረቀት...

በጋዜጣ ላይ እያነበብኩ ነበር፣ (በጭራሽ፤ አልተነገረኝም) ኦራል ሮበርትስን ሲተቹት፣ የጸለየላት የስኳር በሽታ ታማሚ ሴት መሞቷ ነው። እኔም፣ አሁን፣ አሜሪካዊ እንደመሆኔ መጠን፣ ህ—ህጎችንና ባለሥልጣናትን ማዳመጥ እ—እወዳለሁ። ይህ ግን ፍትሐዊ አይደለም። ዶክተሮች ያልቻሉትን፣ ኦራል ሮበርት ጸልዮላቸው የተፈወሱትን ሁሉ፣ በጋዜጣው ላይ ለማስፈር፣ ፍቃደኛ ቢሆኑ ብዬ እጠይቃለሁ። አንድ ጊዜ ቀይረው ይህን ቢጽፉት ብዬ፣ ራሴን እጠይቃለሁ፣ እያችሁ። ቢሆንም እያደርጉትም። ምናልባት ዲያቢሎስ ግራ አጋብቷቸው ይሆናል ብዬ አስባለሁ፣ ይህም፣ በፍርድ ቀን ለድርጊታቸው መልስ ይሰጡበት ዘንድ፣ እግዚአብሔር እንደዚያ እንዲያደርጉ የፈቀደው ነው። ነገር ግን ኦራል ሮበርትስ የጸለየላቸው፣ በሞት አፋፍ የነበሩትን፣ ከዚያም ደህና የሆኑትን በሺዎች የሚቈጠሩ ሰዎችን አውቃለሁ።

10 ስለዚህ፣ እያችሁ፣ እነሱ፣ በዚህ ነገር ትክክል አይደሉም። የራሳቸውን ሃሳብ፣ የትችት ሃሳባቸው ያቀርባሉ፣ ሌላኛውን ጎን ግን እያቀርቡትም።

አሁን፡ ጋዜጣው ወቅታዊ የሚከሰቱትን ክስተቶች ለሕዝብ በጊዜው-ማሳወቅ-ይጠበቅበታል። ከዚያም እኔ እንደማስበው፡ የሰው ልጆች እርስ በርሳቸው የሚተሳሰቡ ከሆነ፡ አንድ ሰው ቢፈወስ፡ በእውነትም ቢፈወስ፡ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ያሉ ሁሉም ጋዜጦች ስለዚህ ጉዳይ ጽሁፎችን ማዘጋጀት አለባቸው። ነገር ግን ይህን እንዲያደርጉ ልትቀጥሯቸው አትችሉም። በጭራሽ። እንደዚህ አይነት ነገር እንዲጽፉ ከወሰዳችሁ፡ ይሳለቁበትና ቀልደው፡ ወደኋላ ይመልሳሉ። አሁን ግን እንዲህ ያለ ነገር ሰተች... ይህች ሀገር ለፍርድ ዝግጁ መሆኗን ያሳያል። በትክክል። ፍርድ መኖሩ የማይቀር ነው፡ ማምለጫም የለም። ብቻ በራሳቸው ላይ እሳትና፡ የመሳሰሉትን እየከመሩ ነው። እንዲህ—ያለ... ከጋዜጣ መርሆዎች ጋር፡ የማይስማማ! አንድ ጋዜጣ፡ መርሆዋቹ፡ የ—የሚሆነውን መልካምም ሆነ መጥፎ ነገር፡ ለሕዝብ ማሳወቅ ነው። እነሱ ግን ከመሰረታዊ መርሆዎቻቸው ርቀዋል። ከመሰረታዊ መርሆዎቻቸው ሲርቁ፡ ዓላማቸውን በ—በደንብ አያገለግሉም።

11 የቤተክርስቲያን ነገርም እንዲሁ ነው። ቤተክርስቲያን ከመሰረታዊ መርሆዎቿ ከራቀች፡ ቅዱሳንን በደንብ ማገልገል አትችልም። አብረን መቄየት፡ አንድ መሆን ይኖርብናል። በአንድ ልብ እና በመስማማት መሆን አለብን። ካልሆነ፡ በመጽሐፍ ቅዱስን መርሆዎች፡ እግዚአብሔር ትክክል ነው ባለው ነገር ላይ ለመቆም፡ በአንድነት ካልተስማማን በስተቀር እግዚአብሔርን ወይም ሕዝቡንማገልገል አንችልም። ሁል ጊዜ ከጎናቸው መቆም አለብን።

12 ቢሊ በቺካጐ ውስጥ፡ አንድ ክፍል ውስጥ ገብቶ፡ እ... አንድ ሰው ወደ እሱ መጣ፡ አንዲት ሴት ከባለቤቷ ጋር፡ በሳንባ ካንሰር፡ እየሞተ ነበር። ሚስቱም በዊልቼር ወንበር ላይ ተቀምጣ የፖሊዮ በሽታ ተጠቂ ነበረች፡ በሳንባ ካንሰር ምክንያት መቆም የማይችልን ባሏን፡ ለመንከባከብ ስትሞክር ነበር። ቢሊም፡ "እ—እዝናለሁ፡ ወዳጄ፡" አለው። አለውም፡ "የጸሎት ካርድ ብሰጥህ ደስ ባለኝ።" "የቀረ ሌላ ካርድ ግን የ—የለኝም፡" አለው።

13 እሱም፡ "ይሁን፡ ችግር የለውም፡ ልጄ" አለው። "ምንም ችግር የለውም፡" አለው። "እዚህ ለመድረስ ሞክረናል፡ ለእኛ ግን እጅግ አስቸጋሪ ነው፡" አለው።

14 ቢሊ እንዲህ አለ፡ "ማድረግ ያለብህን እነግርሃለሁ።" ስለዚህ፡ "አባቴን አመጣዋለሁ። ወደ ውስጥ አመጣዋለሁ፡ ከዚያም አወጣዋለሁ።" እንዲህም አለ፡ "ይህን ሳደርግ፡ መልዕክቱን እንደሰማህ፡" አለም፡ "ከ... ከዚያም አንተና ሚስትህ፡ እኔ ወደምገባባት ትንሽ ክፍል ግቡ፡ እኔም ስለ እናንተ እንዲጸልይ አደርጋለሁ።"

15 እርሱም "ኦህ፡" አለ፡ "ልጄ ሆይ፡ ይህ ድንቅ ነው። በቂ ነው።" አያችሁ? እንዲህ አይነት—አግባብ አለው። አያችሁ? "በቂ ነው። ጥሩ ነው።" አያችሁ?

16 በዚያም ምሽት፡ ቢሊ፡ ወደ ኋላ ተመልሶ በሄደ ጊዜ፡ አሁንም ከተነጋገሩት በተቃራኒ፡ ከሳንባው ደም እየፈሰሰበት የነበረ-የሚስቱ-ወንድም እዚያ ነበር። ሌላም በቁስለት፡ ከሆዷ ውስጥ ደም እየፈሰሰባት የነበረችው የሚስቱ-ወንድም-ባለቤትም፡ በዚያ ነበረች፡ እነሱም አብረዋቸው ሲመጡ፡ ወደ ውስጥ እንዲገቡ አገዛቸው። ይህን ተመልከቱት፡ ክፍሉ ሙሉ በሙሉ ሞልቷል፡ አያችሁ። ነገር ግን ለእነርሱ ከጸልይን በኋላ፡ በደብዳቤ፡ መልዕክት ተቀብለናል፡ ይህም ሰውየው ከሳንባ ካንሰር ሙሉ በሙሉ እንደተፈወሰ

ነው። ሴትየዋ፡ ከዊልቼር ወንበር፡ ተነሰታ፡ እንደወትሮዋ መራመድ ጀምራለች። በሳንባ ነቀርሳ ምክንያት፡ የ—የደም መፍሰስ ያጋጠመው ሰውዬ፡ ሙሉ በሙሉ ደኅና ሆኗል። ሚስቱም ከአንጀት ቁስለት ተፈወሰች። አራቱም በትክክል፡ ተፈውሰዋል! ጋዜጦች ይህን ለማተም ፈቃደኞች ይሆኑ ይሆን ብዬ እጠይቃለሁ። አያችሁ? አያችሁ? አያችሁ? ኦህ! ነገር ግን እግዚአብሔር አሁንም እግዚአብሔር ነው። በራሱ መንገድ ነገሮችን ያደርጋል፡ ታውቃላችሁ፡ መንገዱም መልካም ነው። እርሱ አምላክ መሆኑን በማወቃችን በጣም ደስተኞች ነን።

17 በቀደም ጠዋት ስለምናውቀው ሰለ አንድ ምስኪን ሰባኪ እየተነጋገርን ነበር፡ እርሱም እየዞረ፡ ለታመሙት እና ለሌሎች ይጸልይ ነበር። ሄዶም በሉዊሰቪል ሆስፒታል ውስጥ ሰለ አንዲት ሴት ጸለየ፡ የሳንባ ነቀርሳ በሽታ ነበረባት፡ ሴትየዋም ሞተች። ምስኪኑ ሰውዬ እንዲህ አለ፡ “እይ፡ መጸለይ አያስፈልግም… እግዚአብሔር… እግዚአብሔር የለም። ቢኖር ቃሉን ይጠብቅ ነበር” አለ። እንዲህም አለ፡ “መጽሐፍ ቅዱስ እ—እንዳዘዘው አድርጌ ቀባኋት። ቃሉን የማይጠብቅ ከሆነ፡ አምላክ አይደለም” አለ። “ተራ መጽሐፍ ነው፡” አለ።

18 እንግዲህ፡ እግዚአብሔርን ካላወቃችሁት በቀር እንዲሁ ሊመስል ይችላል። ይህም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነውና፡ መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ ግን አይደለም። ይህም በግለሰቡ እምነት ላይ የተመሰረተ ነው። አያችሁ?

19 ለባለቤቴ ነገርኳት፡ እንዲህ አልኳት፡ “እንግዲህ መኖራቸውን የማውቃቸውን፡ ብዙ የተፈጸሙ ነገሮች አሉ። እኔ በመጨረሻ ምን እንደሚፈጸምብኝ ግን አላውቅም። እኔም በዚሁ መልኩ ልሄድ እችላለሁና። እግዚአብሔር የምሕረት እጁን ከእኔ ላይ የሚያነሳ ከሆነ፡ በዚሁ መልኩ መሄዴ አይቀርምና። የምህረትና የሚመራኝን እጁን በእኔ ላይ እስካቆየ ድረስ ግን፡ እቀጥላለሁ።” ነገር ግን ሜዳን ጠየቅኳት፡ እንዲህ አልኳት፡ “ያ ቀን ጠዋት ትንሿን ልጄን ሳሮንን በራእይ ካየኋት በኋላ፡ በክፍሉ ውስጥ የነበረው ማን ነበር” አልኳት?

20 በነገራችን ላይ፡ በቀደም፡ ራሴን ልስት ነበረ። መንገድ ላይ ተቀምጬ ነበር። ከዛ በኋላ ስለ እርሷ ያየሁትን ራዕይ፡ ታሪኬን ታውቃላችሁ። እና ቀና አልኩና፡ እዚህ በጄፈርሰንቪል ጐዳናው ላይ አንዲት ወጣት ሴት፡ አጠገቤ መጣች፡ ልክ በራእይ ላይ እንደነበረ ነበር። እጆቼን እንዲህ አጠላልፌ ነበርኩ። ትንሿን ልጄ ሳሮንን ትመስላለች! በዚያን ጊዜ ወጣት ሴት ነበረች።

21 ከዚያ ራእይ በኋላ በዚያ ጠዋት፡ ወደ ክብር ተወሰጄ፡ ሆ… ሆፕ እየነገረችኝ፡ እጇን በትከሻዬ ላይ አድርጋ ነበር፡ እሷም “ቢሊ፡ ሰለ እኛ አትጨነቅ። እኛ የተሻለ ነገር ላይ ነን፡” አለችኝ። ያኔ እኔ ራሴን ለመግደል እየሞከርኩ ነበር። እሷም፡ “አትጨነቅ። ከዚህ በኋላ እንደማትጨነቅ ቃል ግባልኝ” አለችኝ።

22 እኔም፡ “ሆፕ፡ ይህን ቃል መግባት አልችልም፡ ምክንያቱም እ—እ—እጨነቃለሁ። ምንም ማድረግ አልችልም፡” አልኳት።

23 እኔም ከራእዩ ሰወጣ፡ በጨለማው ክፍል ቆሜ ነበር። ራእይም አይደለም፡ የምናብ ነገርም አልነበረም፡ ነገር ግን እጇ አሁንም በላዬ ነበር። እየዳበሰችኝም

ነበረች። እኔም አሰብኩት፡ “ቆይ። ይህ ሊሆን አይችልም... ” ያን ጊዜ፡ ራእይን ምን ብዬ እንደምጠራው አላውቅም ነበር። ሰመመን ብዬ እጠራው ነበር። እኔም አልኩኝ “እነሆ... አሁንም እጇ በላዬ አለ፡” አልኩ። “ሆፕ፡ እዚህ ነሽ? ” አልኳት፡

24 እርሷም፡ “ቢል፡ ከእንግዲህ ሰለ እኔና ሰለ ሳሮን እንደማትጨነቅ ቃል ግባልኝ” አለችኝ። ምክንያቱም፡ የጉዞዬ ፍጻሜ ላይ ደርሼ ነበርና። ራሴን ላጠፋ ተዘጋጅቼ ነበር።

እኔም፡ “ቃል እገባልሃለሁ” አልኳት። እሷም አቅፋኝ፡ በእጇ ደባበሰችኝ።

ከዚያም እ—እንዲህ አልኳት፡ “ሆፕ፡ የት ነሽ? ” መብራቱ ላይ ያለውን ትንሽ ሰንሰለት ጎትቼ መብራቱን እስከማበራው ድረስ፡ በጨለማ መ... መፈለግ ጀመርኩ። እዚያ ተቀምጣ እንደሆነ፡ ለማየት ዞርኩኝ፡ በየወንበሩ ፈለግኳት።

እርሱ አምላክ ነው። ዛሬም፡ ያው አምላክ ነው፡ በታቦር ተራራ ላይ ሙሴና ኤልያስ በተገለጡበት እንደነበረው ሁሉ ዛሬም ያው ነው። አሁንም አምላክ ነው።

25 ብዙ ችግሮችና ፈተናዎች ሊያጋጥሙን ይችላሉ። መንገዳችንን ብርሃን፡ ነገሩንም እውን ማድረግ የሚችል፡ አካል መኖሩን፡ ይሄን አትርሱ። ከአድማስ ማዶ ምን እንዳለ አላውቅም። ወደ ታላቁ ጥሪ ወደ ምልክቱ እየዘረጋሁ እንደሆንሁ ግን፡ ይህን አንድ ነገር አውቃለሁ፡ አንድ ቀን ለመፈጸም ሰለተዘጋጀች ታላቋ ክሰተት ለመኖር፡ ዘወትር እታገላለሁ እርሱን ፊት ለፊት፡ እያየሁት፡ “በጸጋ ድኛለሁ፡” ብዬ ታሪኬን የማወራባት ቀን። የምኖረው ለዚያ ቀን ነው። እነዚያን ነገሮች ወደ ኋላ ትቼ፡ መቀጠል እፈልጋለሁ፡ ዝም ብዬ፡ መቀጠል እፈልጋለሁ።

26 አሁን እናንተ በእግራችሁ ያላችሁ፡ ይህ ተበርናክል፡ ወደ ታላቁ ጥሪ ምልክት እንድትዘረጉ እፈልጋለሁ። በምታደርጉት ነገር ሁሉ፡ አብራችሁ ሁኑ፡ በተቻላችሁ አንድ ጎሣ ሁኑ፡ ሁሌም እጃችሁን ሌላ ሰው ለማግኘት፡ ለማምጣት፡ ዘርጉ። ነገር ግን አሁን ከምንሰብካትና በቅንነት ከምንታገልላት እምነት፡ ከእርሷ አንድም ኢንች አትራቁ። ምክንያቱም፡ የእርሱ አገልጋይ እንደሆንኩ ካመናችሁ፡ የእግዚአብሔር ፕሮግራም ይህ ነው። መቼም ቢሆን በብዙኃን ውስጥ አይገኝም። ሁልጊዜም በታናሽ መንጋ ውስጥ ይሆናል፡ ድሮም ነው ሁልጊዜም ይሆናል። ነገር ግን፡ “አንተ ታናሽ መንጋ፡ አትፍራ፣ መንግሥቱን ሊሰጣችሁ የአባታችሁ መልካም ፈቃድ ነው፡” ተብሎ እንደተጻፈ፡ አስታውሱ።

27 አሁን፡ ደግሞ በቤተክርስቲያናችን ውስጥ የተለያዩ የአገልግሎቶች ዘርፎች አሉ፡ ዲያቆናት፡ ባለአደራዎች፡ የሰንበት ትምህርት ቤት ኃላፊዎች፡ ፓስተሮች፡ ቤተክርስቲያናችን በሥርዓት የተደራጀች በመሆኗ እነዚህ ነገሮች አሏት። እናንተም፡ ሰዎች ሆይ፡ እነዚህን አገልጋዮች እና ፓስተር መርጣችኋል። እኔ ምክርና የመሳሰሉትን ለመሰጠት፡ ሁሉም ነገር በትክክል እንደሚሄድ ለማየት፡ የበላይ ተቆጣጣሪ ብቻ ነኝ። ፓስተራችሁን የምትመርጡት እናንተ ናችሁ፡ ባለ አደራዎቻችሁ የምትመርጡት እናንተ ናችሁ፡ ዲያቆናችሁን የምትመርጡት እናንተ ናችሁ፡ በዚህ ቤተክርስቲያን ውስጥ ያለውን ማንኛውንም ኃላፊነት የምትመርጡት እናንተ ናችሁ፣ እናንተ ሰዎች፡ ራሳችሁ። ይኸውላችሁ፡ እነዚህ ሰዎች ይሳሳታሉና፡ በጎናቸው መቆም ግዴታችሁ ነው። ሟቾች ናቸውና። ሰዎች ብቻ ናቸው፡ ይሳሳታሉም። የዩናይትድ ሰቴትስ ፕሬዚዳንት ስሕተት

ቢስራ፡ ከፕሬዚዳንትነት፡ እናስወግደዋለንን? ስህተቱን ረስተን እንቀጥላለን። ቤተክርስቲያናችንን ማስተዳደር ያለብን በዚህ መንገድ ነው። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት፡ ለእነዚያ ዲያቆናት፡ ሲጸልይ እየሰማሁት ነበር። እዚያም በሩ ላይ ሆኖ፡ ከባለአደራዎቹ፡ የተሰጠውን የምስክርነት ቃል፡ ሁላችሁም እንዴት በአንድነት እንደሆናችሁ፡ መስማት ደስ የሚል ነገር ነው። አሁን በዚህ መንገድ ኑሩ። አሁን፡ እናንተ አባላት የሆናችሁ ከባለአደራዎች፡ ከዲያቆናትና፡ ከፓስተር ጎን ቁሙ። አስታውሱ፡ ይህንን አንድ ላይ ስታደርጉ፡ መለያየትን መመልከት የዲያብሎስ ነገር እንደሆነ አስታውሱ። ይህም ሁልጊዜ ነበረ ሁልጊዜም ይሆናል። ነገር ግን እናንተ በአገልጋዮቻችሁ ጎን ቁሙ፡ ለመናገር የፈለግሁት ነገርም ይህ ነበር።

28 ከ... ከዚህም በተጨማሪ ዛሬ ጠዋት ስለ ቦርዶች ስብሰባ እና ስለ ሥልጣናቸው፡ ማስታወቂያ ስሌዳ ላይ የምጽፈው ነገር አለኝ። በማስታወቂያ ስሌዳው ላይ ይሆናል። ለ-... ለባለአደራዎች ሃላፊ ለወንድም ሮበርስን፡ አንድ ኮፒ አምጥቼለታለሁ። ከዚያም ለወንድም ኮሊንስ አንድ ኮፒ፡ የዲያቆናት ቦርድ ሊቀመንበር ይመስለኛል፡ ለእርሱም አንድ አምጥቼለታለሁ። አሁንም፡ እነዚህ ሁሉ ጽሕፈት ቤቶች ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት የተቀመጡ ናቸው፡ ማድረግ ያለባቸውን የቅዱሳት መጻሕፍት ህጎች ሊኖራቸው ይገባል። ስለዚህ፡ ባለአደራዎች የራሳቸው ጽሕፈት ቤት አላቸው። ዲያቆናትም የራሳቸው ጽሕፈት ቤት አላቸው። የሰንበት ትምህርት ቤት የበላይ ተመልካች የራሱ ጽሕፈት ቤት አለው። መጋቢውም የመንጋው ራስ ነው።

29 አሁን፡ እያንዳንዳቸው የሚያመሳስሏቸው ነገሮች አሉ። ሰብሰባችሁም አንድ ላይ መሆን አለበት ብዬ አላምንም፡ እያንዳንዱ ግን እንደየ ጽሕፈት ቤቱ ይሁን፡ ምክንያቱም የሚያቀርቡላቸው ጉዳይ ከሌላቸው በቀር ዲያቆናት ለባለአደራዎች እንዳች ሊሏቸው አይገባም። እነዚያም እንዲሁ፡ ባለአደራዎች የህንጻው ፋይናንስና ሌሎች ነገሮችን ይቆጣጠራሉ፥ ከዲያቆናት ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም። ዲያቆናትም የቤተክርስቲያኑ ፖሊሶችና፡ የፓስተሩ ረዳቶች ናቸው። ባለአደራዎች የንብረቶችን ሁሉ ያዥ ናቸው። ባለአደራዎች ከመንፈሳዊ ነገር ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም፡ ዲያቆኑም ከፋይናንስ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ስለዚህ፡ ግዴታ እንደዛ መሆን አለበት። የሰንበት ትምህርት የበላይ ተመልካች ደግሞ የሰንበት ትምህርትን መከታተል አለበት። ስለዚህ ማስታወቂያ ስሌዳው ላይ፡ እንዲታይ ሁሉንም ነገር እጽፈዋለሁ፡ እለጥፋለሁ።

30 ከዚያም ደግሞ ቤተክርስቲያኗ የምትደግፈውን ዶክትሪን፡ እዚህ ቤተክርስቲያን ውስጥ፡ በፍሬም እናስቀምጠዋለን፡ የምንቆምለትን፡ መ—መርሆቻችንን፡ የቤተክርስቲያን ትምህርት፣ በቤተክርስቲያን፡ በፍሬም እናስቀምጠዋለን። አሁን፡ ቤተክርስቲያን ለመባል፡ ዶክትሪን ሊኖረን ይገባል።

31 "**እዚህ** ድረስ እንሄዳለን፡" እያልን፡ ምንም ድምበር አናበጅም። እግዚአብሔር በቅዱሳት መጻሕፍቱ ውስጥ፡ ከሕዝቡ ጋር እንድንሄድ፡ የሚፈቅድልንን ያህል ብቻ፡ ከሰው ሁሉ ጋር፡ በመተባበር እንሄዳለን። አሁንም አንድ ላይ ተጣብቃችሁ፡ በአንድነት፡ በአንድ ልብ ሁኑ፡ ከእግዚአብሔር ጋር ወደፊት ቀጥሉ። እግዚአብሔር እንድናደርግ የሚፈልገው ይህ ነው።

አሁን እንጸልይ፡ ከዚያም ቃሉን እናነባለን።

32 ውድ ጌታ ሆይ፡ እነሆ አሁን ወደ መለኮታዊው ቃል እንቀርባለን፡ ወይም ቃሉን እናነባለን። መንፈስ ቅዱስህ ለእኛ የሚያስፈልገንን ሁሉ ይተርጉምልን። ጌታ ሆይ፡ በጸጋህ እንደጠራኸን፡ ሁላችን ልጆችህ መሆናችንን አውቀን፡ እንድንናገር፡ እንድንሰራና፡ እንድንኖር አድርገን። ይህም ወደ አንድ ታላቅ እንቅስቃሴ የምንገባበት ጊዜ ላይ መሆናችንን በማየት፡ በዚህ ቤተክርስቲያን ውስጥ ህብረት ይኑር፡ ሌሎች አገልጋዮችን በማፍራት ወደተለያዩ ክፍሎች መላክ እንዳለብን፡ ይሰማናል፡ ይህም ወደ ተለያዩ የዓለም ክፍሎች ብትልከኝ፡ እምነትን ለማቋቋም፡ ኃላፊነቱን ለመውሰድ የሰለጠነ፡ ዝግጁና ፈቃደኛ የሆነ አገልጋይ እንዲኖረን እፈልጋለሁ። አንዴ ለቅዱሳን የተሰጠውን እምነት፡ በጀግንነት የምንቆምለት ይሁን፡ በዓለም ዙሪያ ጸንቶ ይቁም። እርዳን፡ ጌታ ሆይ። ጌታ ሆይ፡ ያኔ በዚህ ሰፍራ ቤተክርስቲያን ይተከልበት ብለን፡ ይህ ቋጥኝ የበዛበት ሰፍራ፡ ለአንተ አደራ በሰጠነው ጊዜ እንደነበረ፡ ከእርሷ አገልጋዮችና ወንጌላውያን እና አስተማሪዎችና ሚሰዮናውያን ወጥተው፡ ወደ ሁሉም የዓለም ክፍሎች ይሂዱ።

33 ዛሬ ጠዋት፡ አሁን እየተሰቃዩ ላሉት፡ ለወንድማችንና ለእህት ስቲከር ልዩ በረከት እንጠይቃለን። ነገር ግን ሁላችንም በእነዚህ ፈተናዎች ውስጥ እንደምንገባ እናውቃለን። ወደ እግዚአብሔር የሚመጣ ልጅ ሁሉ ሊገሠጽ፡ ሊፈተን ይገባልና። በቀላሉ ተሰፋ የምንቆርጥና፡ ወደ ኋላ የምንመለስ ከሆነ፡ ዲቃላዎች ልጆች ነን እንጂ፡ የእግዚአብሔር ልጆች አንሆንም። ለወንድምና ለእህት ስቲከር ኃላፊነታቸውን ለመወጣት፡ የሚያስችላቸውን ጥንካሬና ኃይል ሰጣቸው። የሚበሉትን ምግብ እየለመኑ ከሆኑ፡ የበረከት ክንድህ በእነሱ ላይ ትሁን። እናውቅም ነገር ግን ምናልባት በዚያ ምክንያት ለአፍሪካ ተወላጆች እውነተኛ ክርስቲያን ምን እንደሆነ ለማሳየት ሊሆንም ይችላልና። እርዳን፡ ጌታ ሆይ። አሁን ሁሉም ነገር እንደ ፈቃድህ ይሁን።

34 ይህን ፓስተር፡ ወንድም ኔቪልን ባርከው። ጌታ ሆይ፡ እንደቀድሞው፡ የጉባኤው እረኛ አድርገህ እንድትሾመው፡ እንጸልያለን። በተጨማሪም በጣም የታመመችውን ፍቅር የሆነችውን፡ ምስኪን ባለቤቱን አንረሳትም። ጠላት ወንድም ኔቪልን ከልጆቹ ጋር፡ ያለ እናት እንዲኖሩ ቢፈልግም፡ እኛ ግን በእምነት፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ደም በጠላት እና በእኅታችን መካከል፡ እናስቀምጣለን። ጌታ ሆይ፡ ሁሉም ሴቶች በዚህ ዘመን ጨለማ፡ በሸለቆ ውስጥ እንዲኋዙ የተወሰኑ መሆናቸውን በማወቅ፡ መንፈስህ፡ በላዩዋ ታላቅ ይሁን፡ ነገር ግን ከእሷ ጋር እንድትሆን እንጸልያለን። እነዚያን ትናንሽ ልጆችን ባርካቸው። አሁን ፈርታና፡ ተጨንቃ ሊሆን ይችላል፡ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ሁል ጊዜ፡ ለዚያ ቤተሰብ፡ በምሕረት በር ላይ ይሁን።

35 የባለአደራዎች ቦርድ፡ ወንድማችን ዉድ፡ ወንድማችን ኢጋን፡ ወንድማችን ሮበርሰን፡ ሌሎቹንም ሁሉ፡ ጌታ ሆይ ባርካቸው። ዲያቆናት፡ ባለአደራዎች፡ በቤተክርስቲያኗ ውስጥ ያሉ ሁሉ፡ ጌታ ሆይ፡ በቅድስናና በ—በጽድቅ የሥልጣን ዘመናቸውን እንዲያሳልፉ ዘንድ፡ እንጸልያለን። ጌታ ሆይ፡ ባለፉት ዘመናት ያገለገሉትን፡ ባርካቸው። ከሁላችሁም ጋር እንድትቀጥል እንጸልያለን፡ ይህም የአንድነት፡ የመንፈስና የጌታ ፍቅር ያለባት ቤተክርስቲያን በመባል እንታወቅ ዘንድ ነው። የተጻፈውን ቃልህን ስናነብ፡ እንደ አስፈላጊነቱ፡ ቃልህን እንድትሰጠን እንጸልያለን። በኢየሱስ ስም እንጠይቃለን። አሜን።

36 ጸሎት ላይ ሆኜ፡ በረከቱን እያሰብኩ ነበር ወይም ለአዳዲስ የባለአደራዎች ቦርድ እና ለ... ለሌሎች ሁሉ በረከት እየለመንኩላቸው ነበር፡ ከዚህ በፊት፡ በደንብ ያገለገሉትን፡ እነ ወንድማችን ፍሊማን እና እነ ወንድማችን ዴይዝማን እና እዚህ የተቀመጡትን እያሰብኳቸው ነበር። እግዚአብሔርን በታማኝነት ስላገለገሉት ማመስገን እንፈልጋለን። ጌታ ሁል ጊዜ ይባርካቸው፡ ይርዳቸው ዘንድም ከእነርሱ ጋር ይሁን። እ... አሁን እስታውሱ፡ የነገርኳችሁን የማስታወቂያ ስሌዳውንና የመሳሰሉትን፡ ቀጣይ የሚመጡትን ሰብሰባዎችን አስታውሱ።

37 ዛሬ ጠዋት፡ ከእኛ ጋር በመሆናችን ደስተኞች ነን... ደኅና፡ እንዲህ ብዬ ልግለጸው፡ ባለፉት ጊዜያት፡ ለእኔ የተወደደ የነበረ፡ አሁንም ውድ የሆነ፡ ጥሩ ወንድም፡ ፍሬድ ሶትማን፡ ከ... ከሚስቱ ጋር፡ ከሳስካችዋን፡ ካናዳ፡ እዚህ ከእኛ ጋር ለመቆየት እዚህ መጥቷል፡ በሀገራችን ውስጥ፡ ለጊዜው የተቀመጠ፥ በህብረታችን ውስጥ ግን፡ የተወደደው ወንድማችን፡ ወንድም ፍሬድ ሶትማን እዚህ ተቀምጧል። በካናዳ በነበርኩበት ጊዜ ኮንፈረንሱን ያስተባብርልኝ ነበር።

38 ሌላኛው የተወደደው ወንድም ደግሞ ቀደም ሲል ካናዳዊ የነበረ፡ ነጋዴ የነበረ ሲሆን፡ ከእግዚአብሔር በላይ ማንም ቸር-ሊሆን እንደማይችል ለዓለም አረጋግጧል። እርሱና ወዳጁ፡ ለግንባታ ወይም ለውጭ ተልእኮ የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርግ፡ ድርጅት አቋቋሙ። እነሱም ወደ ኦክላንድ ለሰብሰባ፡ ጠሩኝ፡ ገንዘብም እንዳዘጋጁ ነገሩኝ። በፋውንዴሽናቸው፡ ሁሉንም ስፖንሰር ለማድረግ ጠሩኝ።

39 እኔና ወንድም ፍሬድ ወንድም ፍሬድ በነበረው የተወሰነ ገንዘብ ያንን ለማድረግ ሞከርን፡ ያም እኔ በግለሰብ ደረጃ አልወሰደውም። ስለዚህ ለካናዳ ሕዝብ መስጠት እንዳለብንና ምንም መባ እንኳን መቀበል እንደሌለብን ወሰንን፡ ነገር ግን ነገሩ ጥሩ አልሆነም። ሰብሰባዎቹ ጥሩ ነበሩ። መባ ስላልተቀበልን ግን ትንሽ... ቤተክርስቲያኑ መቶ ቢሊዮን ዶላር ዋጋ ቢኖረውም ግድ አይሰጠኝም፡ አሁንም ለእግዚአብሔር፡ ባለ ዕዳዎች ናችሁና፡ መባ መሰብሰብ አለባችሁ። ይህም የአምልኮው አንድ ክፍል ነው። እናንተም ያንን ትዘርፉላችሁ... ምንም እንኳን ገንዘብንና የመሳሰሉትን ነገሮችን ላይ፡ ተቃዋሚ የነበርኩ ቢሆንም፡ አንድ ሰው ስሕተት ሲሠራ፡ ስህተቱን አምኖ መቀበል እንዳለበት ተገንዝቤያለሁ፡ ምክንያቱም እኔና ወንድም ፍሬድ ብዙም ጥሩ እንዳልሆነ ተመልክተናል።

40 እናም፡ ወንድም ቦርደርስ፡ ወንድም ፍሬድን ትቼ ወደ ኦክላንድ ወደ አንተ ስመጣ፡ እንዲህ አልኩህ፡ "እንደዚያ እንዳታደርግ። የመባ መቀበያውን ሳህን አዙር፡ መባም ተቀበል፡ እና፡ ምንም ይሁን ምን፡ ለሌላ ሰብሰባ በፋውንዴሽንህ መልሰህ አሰቀምጠው" አልኩህ።

41 አገልግሎቱ ከመጠናቀቁ በፊት፡ ወንድም ቦርደርና ወዳጆቹ ወደ እኔ መጥተው፡ እንዲህ አሉኝ፡ "ሰ—ሰብሰባውን ለማድረግ የምናወጣው ገንዘብ ሁሉ፡ ቀድሞውኑ ተሰብስቧል።"

42 ከዚያም፡ ከጥቂት ቀናት በፊት፡ በካሊፎርኒያ ሳን ሆሴ ውስጥ፡ ሰብሰባ ለማድረግ ዝግጅት አደረገ፡ በሽለቆው ውስጥ፡ ሰልሳ ወይም ሰባ የሚያህሉ አብያተ ክርስቲያናት ነበሩት ብዬ እገምታለሁ፡ ሁሉም የተለያየ እምነት

ያላቸው ሲሆኑ ሁሉም ይተባበራሉ። ድንቅ የሆነ ስብሰባ አድርገናል፡ እንደገና፡ በህዳር እንመለሳለን። ወንድም ቦርደርስና ወንድም ፍሬድ፡ እዚህ በመሆናችሁ ደስተኞች ነን። እነዚህ ሰዎች ለሁላችሁ እንግዳዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡ በመስኮች ውስጥ ግን የተወደዱ ወንድሞቼ ናቸው፡ ለቆምንበት እምነት በቅንነት ሲታገሉ የኖሩ ናቸው። እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ወንድሜ። ዛሬ ጠዋት፡ እዚህ በትንሿ በድሮዋ ተበርናክል ውስጥ፡ በመገኘታችሁ ደስተኞች ነን። እምብዛም የሚታይ ነገር የላትም። ነገር ግን እዚህ የሆነ ነገር አለ፡ ይህም፡ እግዚአብሔር እዚህ እንዳለ እናውቃለን፡ አያችሁ፡ በዚህም ደስ ይለናል። ዛሬ ለመጥቀስ ጊዜ ቢኖረኝ፡ ሌሎች የተወደዱ ወንድሞችም፡ ከእኛ ጋር አሉ።

43 አሁን በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት ውስጥ፡ ጌታ ከፈቀደ፡ እንደመራኝ ይሰማኛልና… መሄድ እፈልጋለሁ፡ ማስታወቂያውን ገና አልተናገርኩም። ቀጣዩ ስብሰባ፡ ከወንድም ሱሊቫን ጋር፡ ወደ ኦሃዮ ይሆናል፡ በካምፕ ሜዳ ውስጥ፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ እናደርጋለን። አንድ መቶ ማይልስ ገደማ ብቻ ነው፡ ብዬ እገምታለሁ፡ ጂን፡ እንደዛ ይመስለኛል። ለእረፍት ጊዜአችሁ እቅድ ገና አላወጣችሁም፡ ጌታ የሚመራን ከሆነ፡ መልካም ጉዞ ይሆናል። በጣም ጥሩ ሰው ነው፡ ወንድም ሱሊቫንን፡ በጣም እናደንቀዋለን። የ… የከተማዋ ከንቲባ ነው። የቀድሞ-ከንቲባ እሱ ነበር፡ የድሮ-ኬንታኪያዊ ነው። ስለ እሱ ማለት የምችለው ይህ ብቻ ነው። በቀደም ሳገኘው… ሁለታችንም ያደግነው በኬንታኪ ተራሮች ውስጥ ነው። “አሁንም አሳፍቲዳ በአንገትህ ላይ ታሰራለህ እንዴ፡ ቢሊ፡” አለኝ? እና ም——ምን ያህል ኬንታኪ እንደሆነ ታውቃላችሁ። አሁን ዞር እንበልና…

የኬንታኪ ወንድሞቼን፡ ወንድም ጀፈርሪስ፡ የመሳሰሉትን መናቁ አይደለም። እኔም፡ የኬንታኪ ሰው ነኝና፡ እናንተም ታውቃላችሁ። ስለ እኛ አንድ ነገር እነግራችኋለሁ። እኛ ኬንታኪያን አይደለንም፡ አሜሪካኖችም አይደለንም። እኛ እንግዶችና መጻተኞች ነን። ሊመጣ ያለውን ከተማ እየተጠባበቅን ነው።

44 አሁን ለጥቂት ደቂቃዎች፡ ከዘጸአት መጽሐፍ ላይ፡ እናንብብ። ምዕራፍ 23፡ እንዲሁም ከቁጥር 20 እስከ 23 ድረስ ያሉትን ጥቅሶች፡ ማንበብ እፈልጋለሁ። ለዛሬ ጠዋት እንደ ርዕስ መጠቀም የምፈልገው፡ ከዚህኛው፡ ማለቴ፡ ከዚህ፡ **ፍጹም ነጻ መውጣት** የሚል ይሆናል። መጽሐፋችሁንና ምዕራፋችሁን እንድታነቡ በመጠባበቅ ላይ ሳለሁ፡ በንግግር፡ ብዙም አላቆያችሁም።

> **በመንገድ ይጠብቅህ ዘንድ፡ ወዳዘጋጀሁትም ስፍራ ያገባህ ዘንድ፡ እነሆ፡ እኔ መልአክን በፊትህ እሰድዳለሁ።**
>
> **በፊቱ ተጠንቀቁ፡… ቃሉንም አድምጡ፡ ስሜም በእርሱ ስለ ሆነ፤ ኃጢአት ብትሠሩ ይቅር አይልምና፡ አታስመርሩት።**

“ስሜም በእርሱ ስለ ሆነ።” ይህ መልአክ ማን እንደሆነ ጉባኤው እንደሚያውቅ እርግጠኛ ነኝ።

> **አንተ** ግን **ቃሉን** ብትሰማ፡ **ያልሁህንም ሁሉ ብታደርግ፤ ጠላቶችህን** እጣላቸዋለሁ፡ **ተቃዋሚዎችህንም እቃወማቸዋለሁ።**
>
> **መልአኬ በፊትህ ይሄዳልና፡ ወደ አሞራውያንም… ወደ ኬጢያውያንም፡… ወደ ፌርዛውያንም፡…**

**ወደ ከነዓናውያንም:... ወደ ኤዊያውያንም:... ወደ: ኢያቡሳውያንም... ያገባሃል፡ እኔም አጠፋቸዋለሁ።**

45 አሁን ለጥቂት ደቂቃዎች እየተነጋገርን ሳለን ከጸለያችሁ፡ ጌታ ቃሉን ይባርክ። በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ለመናገር እያሰብኩ ነበር፡ ይህም፡ **ፍጹም ነጻ መውጣት** የሚል ነው።

ቤተክርስቲያን ሁሌም—ታናሽ መንጋ ሆና ቆይታለች። ኢየሱስ እስከሚመጣ ድረስ፡ ሁልጊዜም በአባላት፡ ታናሽ ትሆናለች። ኑሮዋ ግን በእግዚአብሔር-በተሰጡ ጸጋዎች ሥር ነው። የምናውቀው አንድ ነገር ቢኖር፡ ይህች የሕያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ናት፣ የብራንሃም ተበርናክል አይደለችም፡ ነገር ግን የብራንሃም ተርናክል የዚያ አካል ብቻ ነው። በአገሪቱ ውስጥ እንደዚህ ያሉ ሌሎች ተበርናክሎች አሉ።

46 ወንድም ስኔሊንግ፡ ዛሬ ማታ፡ የጥምቀት አገልግሎት ያከናውናል። ወንድም ከርቲስ ለማስተዋወቅ የነገረኝን ረሳሁ፡ ትናንት ነው የነገረኝ፡ የጥምቀት አገልግሎት አለው። የጥምቀት ሥነ ሥርዓት እያደረገ ነው። እዚህ ማንም ያልተጠመቀ ሰው ካለ፡ ለምን፡ ወንድም ስኔሊንግ፡ ዛሬ ማታ፡ እናንተን በማጥመቁ ደስ ይለዋል። በኡቲካ የሚገኘው ሆሊነስ ተበርናክል ነው። እንዲሁም በኒው አልባኒ የሚገኘው፡ ወንድም ጁኒየር ጃክሰን። በአገሪቱ ውስጥም ብዙ እንደዚህ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት አሉ። ይብዛም ይነሰም ግን፡ ሁላችንም፡ በተሸናፊው ወገን የምንኖር፡ ይመስላል።

47 ከኋላ ሆኜ፡ ወንድም ኔቪል ዛሬ ጠዋት ማስታውቂያ ሲናገር ሰምቼዋለሁ፡ በዚህም ወደ አእምሮዬ የመጣው፡ ሕዝቡ ነጻ ከመውጣት እየራቁ እንደሆኑ ይመስላሉ። ይህ የሆነ ነገር ይመስላል፡ ይህም፡ ሰዎች አይተውታል፡ ቢሆንም ወደ ጎን ገፍተውታል፡ "ኦህ፡ እነሆ፡ እግዚአብሔር ያደርገዋል።" ይሁን እንጂ ይህ አግባብ አይደለም።

48 አሁን፡ ሙሴ፡ በእግዚአብሔር በተጠራ ጊዜ፡ ፍጹም የሆነ፡ በሙላት ነቢይ ነበር።

እግዚአብሔር አንድን ሰው አንድን ነገር እንዲያደርግ ሲልከው፡ በሚያስፈልገውን ሁሉ በሙላት ያስታጥቀዋል። እግዚአብሔር ሰባኪ እንዲሆን ቢጠራው፡ የሚሰብክበትን ነገር ይሰጠዋል። መምህር እንዲሆን ቢጠራው፡ የሚያስተምረውን ነገር ይሰጠዋል። ነቢይ እንዲሆን ቢጠራው፡ ራእይን እንዲያይና ነቢይ እንዲሆን፡ አንድ ነገር በላዩ ያሰቀምጣል። እግዚአብሔር ሰውን ሁሌም በሙላት ያስታጥቀዋል።

ሙሴን ወደ ግብጽ በላከው ጊዜም ያደረገው ይህንኑ ነው። በሆነ መንገድ አስነሳው። በሆነ መንገድ አስተማረው፡ ቀረጸውም፡ አበጀውም፡ ፍጹምም አደረገው። ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት፡ ለአብርሃም ሕዝቡን ነጻ እንደሚያወጣ፡ ቃል ከገባለት በኋላ፡ ከ—ከዚያም ሙሴ በተፈጠረበት መንገድ ሙሴን ለአላማው እንደሚያደርገው አሰበ። ሙሴ የተሟላ ነቢይ ነበር። ከዚያም፡ የተሟላ ነቢይ ሰለሆነ፡ ከዚያ...

49 ልክ እንደ እናንተ፡ ክርስቲያኖች ሰትሆኑ፡ እግዚአብሔር ግማሽ ክርስቲያኖች አያደርጋችሁም። ሙሉ ክርስቲያኖች ያደርጋችኋል። እግዚአብሔር ግማሽ ሰባኪዎች አያደርግም፡ ሰባኪው ራሱ ግን ግማሽ ሰባኪ ሊሆን ይችላል።

እግዚአብሔር ልጆቹን ክርስቲያን ያደርጋቸዋል፡ አንዳንዴ ግን ግማሽ ክርስቲያን ይሆናሉ። እግዚአብሔር ግን እንዲህ እንዲሆኑ ፍላጎቱ አይደለም። የራሳቸው መንገድ እግዚአብሔር ለሕይወታቸው ካለው እቅድ ጋር ሲቀላቀልባቸው፡ እነሱም እንደዚያ እንዲሆኑ ያደረጋቸዋል። እግዚአብሔር ግማሽ ክርስቲያን እንዲሆኑ፡ ወይም ግማሽ ሰባኪዎች እንዲሆኑ አይፈልግም፡ በሁለት ነገር እንዲያመቻምቹ አይፈልግም፡ ወይም… በክፍተት ሁሉ ጸንተው በሙላት እንዲቆሙ ይፈልጋል።

50 አሁን፡ እግዚአብሔር ሙሴን፡ የተሟላ ነቢይ አድርጎ የሾመው፡ በሙላት ነጻ እንዲያወጣ ነበር። ሙሴም በሙላት ለእግዚአብሔር እጅ አሳልፎ ተሰጠ። ለዚህም ነው እርሱን እንደዛ አድርጎ የሰራው። እግዚአብሔር በእርሱ እስኪታመን ድረስ በእግዚአብሔር የተሟላ ነበር።

51 ዛሬ ጠዋት፡ እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠንን ቦታ፡ እስከሚሰጠን ድረስ፡ እንደ ክርስቲያኖች፡ ፈቃዳችንን ለእግዚአብሔር አሳልፈን የሰጠን፡ እራሳችንን በሙላት ለእግዚአብሔር አሳልፈን የሰጠን ነን ወይ እላለሁ። ዛሬ ጠዋት እኔ ራሴ፡ እግዚአብሔር በእኔ፡ በወንድም ኔቪል፡ በባለአደራዎች ቦርድ፡ በዲያቆን ቦርድ፡ ወይም በቤተክርስቲያናችን አባላት ላይ፡ እምነቱን እስኪያደርግ ድረስ፡ ለእግዚአብሔር ራሴን አሳልፌ መስጠት ችዬ ይሆን ብዬ ራሴን እጠይቃለሁ። ሁላችንም ቦታና፡ ግዴታ አለብን።

52 አገልጋዩ ሰባኪ ለመሆን የተጠራ ከሆነ፡ የክርስቶስን ፍለጋ የለለበትን ባለጠግነት፡ ሳያመቻምች ቆሞ፡ የመስበክ ግዴታው አለበት። ሰባኪ ለመሆን ከተጠራ፡ ለአንድ ሰው ሲል ምንም ነገር ከመናገር አይቆጠብም።

53 የቤተክርስቲያኒቱ አባል ደግሞ፡ የአንድ ቡድን አባል ለመሆን ስለተጠራ፡ በምንም ማመቻመች የለበትም። ቤተ ክርስቲያኒቱ ቁማር መጫወት የለብንም ብላ የምታምን ከሆነ፡ ያ አባል ቁማር የሚጫወቱበትን ካርታዎች እንኳ መንካት የለበትም። በመጠጥ አናምንም፡ ራሱን ከመጠጥ በሙላት ማውጣት አለበት። ቁማር መጫወትንም፡ ሆነ ማጨስን የማናምን ከሆነ፡ የዚህ ቤተክርስቲያን አባል እንዲህ ዓይነቱን ነገር መንካት የለበትም። እግዚአብሔር የተሟላ ነጻ መውጣት ያደርጋል። እኛ…

ራሳችንን ለእርሱ በሙላት አሳልፈን የምንሰጥ ከሆነ ይህን ያደርጋል። ራሳችንን በሙላት ለእጁ አሳልፈን ከሰጠን፡ እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ መኖር ይችላል። የክብር ተስፋ፡ ክርስቶስ፡ የራሳችንን ነገር ከመንገድ አስወግደን ስናስወጣ ራሱን በእኛ ያንጸባርቃል። ከዚያ ሃሳባችን ሃሳቡ ይሆናል። ኢየሱስ ሲጋራ ሲያጨስ መገመት ትችላላችሁን? ክርስቶስ ሲጠጣ፡ ወይም ካርታ ሲጫወት ማሰብ ትችላላችሁ? ስለዚህ መንፈሳችሁ የእርሱ መንፈስ አካል ከሆነ፡ በገዛ ውሳኔአችሁ እንዲሆን ይፈልጋል። እናንተ ግን ዲያብሎስ መጥቶ እንዲቆጣጠር ትፈቅዱለታላችሁ። ሁል ጊዜም፡ በልባችሁ፡ ጥልቅ ውስጥ፡ እነዚህን ነገሮች ሲታደርጉ እንደተሳሳታችሁ ታውቃላችሁ።

አንድ አባል በሌላው አባል ላይ ሲናገር፡ ያ ስህተት እንደሆነ እወቁ። እርስ በርሳችሁ እንድትጸልዩ፡ እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ እንጂ፡ አንዱ በአንዱ ላይ እንድትናገሩ አልታዘዛችሁም። አንድ ሰው ከወደቀ፡ እናንሳው፡ እንርዳው። ያም፡ አንድ የሆኑ የ—የ—የአማኞች ህብረት እንድንሆን ያደርገናል። አሁን፡

ያንን ሳንታዘዝ ስንቀር፡ እግዚአብሔርን ባለመታዘዛችን እግዚአብሔርን እናሳዝነዋለን። ስለዚህም፡ ቤተክርስቲያናችን፡ ህዝባችን ሊበለጽግ አይችልም፡ ቤተክርስቲያኗ ልትቀጥል አትችልም፡ ይህም አንድነት፡ አንድነት የሌለን በመሆናችን ነው። ኢየሱስ ሲናገር፡ “ትንሽ እርሾ ሊጡን ሁሉ ያቦካዋል” ብሏል።

54 ለምሳሌ፡ የቤተክርስቲያኒቱ ቦርድ፡ ወይም እንደ ዲያቆናት—የመሳሰሉ፡ መ... መጥተው አዲስ ተብርናክል መገንባት እንዳለብን እንደሚያስቡ ቢነግሩን። ይህም የዲያቆናት ምርጫ ከሆነ፡ በጉዳዩም ባለአደራዎቹ ሲጠየቁ ይህን ለማድረግ ገንዘብ ከሌላቸው፡ እኛ አሁን እንደምናደርገው ግንባታውን ለማድረግ ፕሮግራም ይኖራቸዋል። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያኒቱ በሙሉ ሉዓላዊ በመሆኗ፡ ስራውን ሙሉ ጉባኤው መወጣት አለበት፡ ብዬ እምናለሁ። ከዚያም ቤተክርስቲያኒቷ ለአዲሱ ተበርናክል መገንባት በሙሉ ድምጽ የምትስማማ ከሆነ፡ ሁላችንም ያንን አዲስ ተበርናክል ለመገንባት አብረን መሥራት አለብን።

55 እውነቱን ለመናገር፡ እኔ ራሴ፡ ስለ አዲስ ተበርናክል ሲነግሩኝ፡ እኔ ራሴ፡ የሃሳቡ ተቃዋሚ ነበርኩ። በትክክል። እንዲህም አልኩኝ፡ “አዲስ ተበርናክል አያስፈልገንም። ያሳየኝ ነገር ከተፈጸመ፡ እንደ ጌታ ከሆነ... በቅርቡ ከዚህ እሄዳለሁ። አዲስ ተበርናክል ምን ያደርግልናል? ለመስራትም ገንዘብ የለንም” አልኩ።

56 ከዚያ ወደዚህ መጣሁና የቤተክርስቲያንቷ ስሜት ተሰማኝ፡ ቤተክርስቲያንቷ፡ በአብዛኛው፡ ተብርናክሉ እንዲሰራ የፈለገች ይመስላል። ከዚያም ምን አደረግሁ? የራሴን ሃሳቦች መሥዋዕት አድርጌ ከቤተክርስቲያን ሃሳብ ጋር ተስማማሁ። ይሁን፡ እንስራው። በ... በዚህ መንገድ ነው ዕጣ የምንጥለው፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜም እንደዛ ነው የሆነው፡ ቤተክርስቲያን ምርጫዋ ይህ ነው። በ—ሉዓላዊነት፡ የሰዎች ቡድኖች፡ አንድ ይሆናሉ። በአንድነት ውስጥ ጥንካሬ አለ። ስለዚህ፡ ከዚያም፡ እንዲህ አልኩ፡ “በእርግጥ፡ ቤተክርስቲያንቷ የምትፈልገው እንዲህ ከሆነ፡ እግዚአብሔር የሚፈልገው እንዲህ ከሆነ፡ እሱ ከእኔ ይልቅ በብዙ ሰዎች መካከል የመምረጥ ሥልጣን አለው፡ ምክንያቱም ይህ መሆን የለበትም የሚል ራእይ የለኝም።” ስለዚህ ከቤተክርስቲያንቷ ጋር እንስማማለን፡ ከቤተክርስቲያንቷም ጋር እንንቀሳቀሳለን። የምችለውን ሁሉ ለማድረግ፡ በተክርስቲያንቷን ለማገዝ፡ ከጀርባዋ አለው፡ አያችሁ።

57 አንድ መሆንና እርስ በርስ መጣበቅ ይህ የእያንዳንዱ ክርስቲያንና፡ የቤተክርስቲያን አባል ተነሳሽነት መሆን አለበት። ቤተክርስቲያንቷ በምትመርጠው ነገር ሁሉ፡ ልንቆም ይገባል። ለምሳሌ፡ እንበልና፡ በ... ቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ የሆነ ነገር መቀየር ፈለጉ። እሺ፡ ከዚያ፡ ባለአደራዎቹ ከፈለጉ፡ ሌ... ሌላ ሰው ከፈለገ፡ ዲያቆናት፡ አንድ ነገር ለመለወጥ ከፈለጉ፡ ወደ ቤተክርስቲያንቷ ይቀርባል፡ ከዚያም ቤተክርስቲያን በጋራ። እና እ—አሳባችን ከጠቅላላው ቤተክርስቲያን ሃሳብ የተለየ ከሆነ፡ ያንን ሃሳብ መሥዋዕት እናድርግ፡ ምክንያቱም አንድ ሆነን መቆም የምንችልበት ብቸኛው መንገድ ይህ ነው። ይህች ቤተክርስቲያን አሁን እየሄደች ባለችበት መንገድ ከሄደች፡ እና በአንድነት ከጸናች፡ እግዚአብሔር... እርስ በርስ ከተያያዝን፡

እሱ የሚያደርገው፡ ገደብ የሌለው ነገር ይሆናል። ግዴታ አንድ ላይ መያያዝ አለብን። እንደዚያ መሆን እንፈልጋለን፡ እርስ በእርሳችን በሙላት መሆን፡ ከዚያም በእግዚአብሔር እጅም በሙላት መሆን።

58 ከዚያም የእግዚአብሔርን ቃል ይሰብካል ብለን የምናምነው ሰው ይኖረናል። ሰውዬው የእግዚአብሔርን ቃል የማይሰብክ ከሆነ፡ የሚሠራ ሌላ ሰው እናገኛለን። እኛ መቆም ያለብን በዚህ መንገድ ነው። የባለአደራው ቦርድ ትክክል የሆነውን ነገር የማይደግፍ ከሆነ፡ ትክክል የሆነውን ነገር የሚደግፍ ሰው መምረጥ የእናንተ ሃላፊነት ነው። ከዚያም ይህን ስታደርጉ፡ ጽናት ይኑራችሁ። ይመለከታችኋል። በዚያ ጽኑ። እናም፡ ሁላችንም፡ አንድ ላይ ሆነን ለአንድ ነገር እንቆማለን፡ ያም እግዚአብሔር ነው።

59 አንድ አባል ስሕተት ቢፈጽም፡ ዝቅ አታድርጉት። እርዱት። አቁሙት። ተሰብሰቡ፡ እርስ በርሳችሁ ተደማመጡ። መጽሐፉ የሚለው ይህንን ነው። አንድ ስሕተት ስንፈፅም፡ ወደ እግዚአብሔር ፊት እንሂድ። በእግዚአብሔር ፊት ከመሄዳችን በፊት፡ ወደ ጎዳነው ሰው ፊት መሄድ አለብን።

60 እኔ ራሴ ያንን ማድረግ ነበረብኝ። ስህተት መስራቴን አውቄው ነበር። እኔ ዋሸሁ፡ ባለቤቴም እንድትዋሽ አደረግኳት። እዚህ ቤተክርስቲያን ውስጥ፡ ስለዚህ ጉዳይ የነገርኳችሁ ይመስለኛል። ከጥቂት ቀናት በፊት፡ በቅርብ ጊዜ፡ ከስድስት ሳምንታት በፊት ይሆናል። ጠበቆቹ በዚህ ምርመራ፡ የት እንዳለሁ እንኳን እስከማላውቅ ድረስ፡ በጣም አበሳጭተውኝ ነበር። እራት ለመብላት ብቻ፡ ከቢሮ ወደ ቤት ሄጄ ነበር። የቤት ስልክ ሲደወል፡ ሜዳ ስልኩን ለማንሳት ሄደች። እጇን በላዩ ላይ አድርጋ፡ “እንደገና እነዚያ ጠበቆች ናቸው፡” አለችኝ።

61 እንዲህ አልኩ፡ “ተጨማሪ ምሽት መቋቋም አልችልም። ጭንቅላቴ ሊፈነዳ ነው። በዚህ፡ እና በዚያ፡ እና በዚያም አቅጣጫ እየጎተተኝ፡ አዕምሮዬን እየሳትሁ ነው።” እንዲህ አልኳት፡ “ይህን ልቋቋመው አልችልም።” ተነሥቼም፡ “እዚህ እንደሌለሁ ንገሪያቸው፡” አልኳት፡ ከቤቱ ጀርባ እየሮጥኩ ሄድኩ።

62 ተመልሼ ስመጣ… ሜዳ ለእነዚህ ነገሮች በጣም ተጨንቃለች። ለማልቀስ ትንሽ ቀርቷት፡ በሩ ላይ አገኘችኝ። “ቢል፡ እንዲህ ማድረግህ ትክክል ነበር? ” አለችኝ፡

63 እንዴት እንደሆንክ ታውቃለህ። እኔ እንዴት እንደሆንኩ አውቃለሁ። እኔም “እርግጥ ነው። በዚያን ጊዜ እዚህ አልነበርኩም፡” አልኳት። እግዚአብሔር በዚህ ምክንያት እንደኮነነኝ አውቅ ነበር። እኔም “በሰአቱ እዚህ አልነበርኩም፡” አልኳት።

“ስልኩ ሲደወል ግን እዚህ ነበርክ፡” አለችኝ።

64 እና በዚያን ቀን ከሰዓት በኋላ ለታመመ ሕፃን ለመጸለይ ወጣሁ። ቤቱን ለቅቄ ከመውጣቴ በፊት፡ ስልኩ እንደገና ተደወለ፡ ትንሹ ጆሴፍ ሮጦ ስልኩን ያዘና እንዲህ አለኝ፡ “አባዬ፡ እዚህ እንዳልሆንክ እንድነግራቸው ትፈልጋለህ? ” ኃጢአት እንዴት እንደሚያበላሽ፡ በመጨረሻም ቤተሰብን ምን እንደሚያደርግ ታያላችሁ?

65 አንደኛ ዮሐንስ፡ ምዕራፍ 5፡ ቁጥር 21፡ እንዲህ ይላል፡ “ልባችን የማይኮንነን ከሆነ፡ በእግዚአብሔር ላይ ድፍረት አለን።” ልባችን የሚወቅሰን

ከሆነ ግን፡ በእግዚአብሔር ላይ ድፍረት እንዴት ይኖረናል? ያልተናዘዝነው ሃጥያት እስካለን ድረስ፡ ፈጽሞ እንደማይሰማን፡ እናውቃለን። ጠንካራ ነው፡ ነገር ግን፡ በ—በ—በቃ ይሄው ነው፡ ቤተ ክርስቲያን እነዚህ ነገሮች ያስፈልጓታል።

66 ከዚያም ለህጻኑ መጸለይ ጀመርኩ። እጆቼን በላዩ ላይ መጫን ስጀምር፡ ጌታ ገሠጸኝና እንዲህ አለኝ፡ “ውሸት ተናግረሃል። ለዚያ ሕፃን ለመጸለይ ብቁ አይደለህም።”

67 ሰውየውን ትቼ ዞር አልኩ። እንዲህ አልኩት፡ “ወዳጄ፡ እዚህ ጠብቀኝ። አንድ ነገር ማስተካከል አለብኝ።”

68 ጠበቃውን ጠራሁና ወደ ቢሮው ወርጄ፡ ጠራሁት። እንዲህ አልኩት፡ “ተመልከት፡ ወዳጄ፡ ዋሽቻለሁ። ባለቤቴም እንድትዋሽ አደረግኳት። ቤት ውስጥ የለም አለች፡ እኔም ከቤቱ ጀርባ በኩል ሄድኩ።” እናም ተናዘዝኩና ነገርኩት።

69 ወደ እኔ መጣና እጆቹን ትከሻዬ ላይ አስቀመጠ። እንዲህም አለኝ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ ሁሌም በአንተ ላይ እምነት ነበረኝ፡ አሁን ግን ከመቼውም ጊዜ በበለጠ፡ ሰው፡” እንዲህ አለ፡ “ስህተቱን ለማረም ፈቃደኛ የሆነ ሰው አገኘሁ” አለኝ።

70 ነገርኩት፡ እንዲህ አልኩት፡ “ለአንድ ሕፃን መጸለይ ጀምሬ፡ ጌታ በልቤ፡ ይወቅሰኝ ነበር፡ ምክንያቱም ስህተት እንደሰራሁ አውቃለሁ።”

71 ከዚያም፡ በቀጣዩ ቀን፡ ባለቤቴ፡ “ወዴት ነው የምትሄደው” አለችኝ?

እኔም፡ “ወደ ዋሻዬ” አልኳት።

72 ከቻርለስታውን በላይ ወዳለው፡ ዋሻዬ ወጣሁ፡ ለብዙ ዓመታት፡ ወደዚያ ስሄድ ኖሬአለሁ። ወደዚያ ገብቼ፡ ቀኑን ሙሉ ጸለይኩ፡ “አምላክ ሆይ; ዳግመኛ እንዲህ ያለ ነገር እንድፈጽም አትፍቀድልኝ። ጌታ ሆይ፡ ይቅር በለኝ፡ ምክንያቱም ለመጸለይ፡ እጆቼን በታመሙ ሰዎች ላይ መጫን ስጀምር፡ ከዚያም ይወቅሰኛል።” ወደ ማታ ሦስት ሰዓት ገደማ፡ ወጣሁ። በዚያም የተጋደመ አንድ ትልቅ ድንጋይ አለ። እኔም በዚያ ድንጋይ ላይ ወጣሁና፡ ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ እጆቼን ከፍ አድርጌ፡ ጌታን እያመሰገንኩ ተመለከትኩ። በዚያም በጣም ጸጥ ያለ ነበር። እኔም፡ “ጌታ ሆይ፡ አ... አንድ ጊዜ በሙሴ አጠገብ ስታልፍ፡ እርሱም እንደተናገረው... እሱን በአለት ንቃቃት ውስጥ በነበረ ጊዜ፡ ያየው የሰው ጀርባ ይመስል ነበር ብሏል።” እኔም፡ “ጌታ ሆይ፡ አሁንስ ትደግመዋለህን? ይቅር እንደተባልኩ አሳውቀኝ” አልኩት። እኔም አልኩ፡ “የምትረዳኝ ከሆነ ወደ አእምሮዬም ግባ... ” እንዲህ አልኩት፡ “ጌታዬ ሆይ፡ በአእምሮዬ፡ በጣም ጠንካራ አይደለሁም።” እንዲህ አልኩ፡ “አ—አንተን ለማገልገል እየሞከርኩ ነው። ልቤን ታውቀዋለህ፡ እኔም... እንዲህ ማድረግ አልነበረብኝም። ይህን ለማድረግ አስቤ አይደለም። ጭንቀላቴ እየወደቀ እንደሆነ ተሰማኝ፡ በጣም ተጨንቄ ነበር፡ ሰይጣንም በያዘኝ ጊዜ በቅጽበት አደረገሁት” አልኩት። እኔም፡ “ይቅርታ ካደረክልኝ፡ ጌታ ሆይ፡ አንተን እንዳይህ አድርገኝ፡” አልኩት።

73 እግዚአብሔር ምስክሬ ነው፥ ልክ ከጐኔ፡ አንድ ትንሽ ቦታ ውስጥ ቁጥቋጦዎች እንደ ነፋስ መሽከርከር ጀመሩ፡ እኔም ባለሁበት ከዋሻው አጠገብ

መጣና፡ በጫካ ውስጥ ወረደ። ኦህ፡ ወንድሜ፡ አእምሮን ሁሉ ከሚያልፍ በላይ የሆነ ሰላም በእኔ ላይ ወረደ፡ አለቀስኩ። አነባሁ። ጮህኩ። ኃጢአቴ ይቅር እንደተባለልኝ አውቃለሁ። እያችሁ፡ ከእግዚአብሔር ጋር ያለኝን ግንኙነት አቋርጬ ስለነበር፡ ልጁን ጸልዬ ነጻ ላወጣው አልቻልኩም።

74 በ... በሚቀጥለው ቀን ከቺካጎ የመጣ አንድ ሰው ነበር። አንድ ታላቅ ሰው ነው፡ ከካቶልክ የተቀየረ ሰው ነው፡ የልቡ ሰሮች እንደ ውስጣዊ ቱቦ ተሞልተው ነበር፡ ለረጅም ጊዜ እነሱን ለመቁረጥ፡ እየሞከሩ ነበር፡ ሊፈቅድላቸው አልፈለገም። በመጨረሻም ቃለ መጠይቅ ተደረገ። በእነዚህ ቃልመጠይቆች፡ ችግር ምን እንደሆነ እስኪለዩ ድረስ ቆዩ። ሰውየውም ወደ ውስጥ ገና እንደገባ፡ መንፈስ ቅዱስ ወደ ሕይወቱ ውስጥ ገብቶ በካቶሊክ ቤተክርስቲያን ውስጥ የመሰዊያ ልጅ በነበረበት ጊዜ ያደረገውን ነገር ተናገረው። እንዲህ አለ፡ “እውነት ነው። በትክክል እውነት ነው።” እንዲህ አለ፡ “ከእኔ ተቃራኒ ነበር ማለትህ ነው? ”

እኔም፡ “በሕይወትህ ውስጥ የማየው ብቸኛው ጥላ ይህ ነው” አልኩት።

75 ወደ ዶክተሩ ተመልሶ ሄዶ ነገረው፡ እንዲህ አለው፡ “እሺ፡ አሁን ሁሉንም ነገር አዘጋጅ፡ ቀዶ ጥገናውን እናደርጋለን” አለው።

76 ዶክተሩ፡ “ይህን የመጀመሪያውን የደም ቧንቧ እንደገና እንፈትሻለን” አለው። ሰመረምረው፡ እንዲህ አለው፡ “ኦፕሬሽኑ አያስፈልግህም” አለው። እያችሁ?

77 ልባችን የሚወቅሰን ከሆነ፡ ሙሉ በሙሉ ነጻ መውጣት እንፈልጋለን። በግማሽ ነገር ላይ የሚታምን፡ ቤተክርስቲያን መሆን አንፈልግም። እውነተኛ ቤተክርስቲያን መሆን አለዚያም ቤተ ክርስቲያን መሆን አንፈልግም። እውነተኛ ክርስቲያኖች መሆን ወይም ጨርሶ ክርስቲያኖች መሆን አንፈልግም። ከመጥፎ ልማዳችን፡ ከኃጢዓታችን፡ ከክፉ አሳባችን፡ ከክፉ ተግባራችን፡ ከቸልተኝነታችን፡ ከሠራነው ነገር ሁሉ ነጻ መውጣት እንፈልጋለን። ሙሉ ነጻነት እንፈልጋለን፡ ሰለዚህ እንዲፀለዩላቸው፡ ሰዎች ወደዚህ ቤተክርስቲያን ሲመጡ፡ እዚህ የተቀመጠው ይህ ትንሽ ቡድን ብቻ ይሆናል( ምናልባት ከመቶ፡ ወይም ከሁለት መቶ አይበልጥም)፡ ነገር ግን እነሱ ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ይሆናሉ። ሰንጸልይም፡ እግዚአብሔር ከሰማይ ይሰማል። እግዚአብሔር በእጆቹ ውስጥ ሊይዘው የሚችለውን ሰው ይፈልጋል፡ እንዲህ ማለት የሚችለውን ሰው፡ “በእሱ ላይ እምነት አለኝ። ይህንን፡ የታመመ አገልጋዬን፡ በጄፈርሰንቪል ወደሚገኘው ብራንሃም ተብርናክል መላክ እችላለሁ፡ ያ የሰዎች ስብሰብ አንድነት አላቸው።” የሆነ ነገር ይሆናል።

78 መልካም፡ አሁን ባለንበት ሁኔታ ምን እንዳደረገልን ተመልከቱ። አንድ ልብና ስምምነት ቢኖረን ኖሮ ምን ያደርግ ነበር? ይህን ማድረግ የምንችልበት ብቸኛው መንገድ፡ ልባችንን በወንድማማች ፍቅር አንድ ማድረግ ነው፡ የቤተ ክርስቲያኒቱን ባለሥልጣናት፡ እንዲሁም ፓስተሩን በመታዘዝ ነው፡ ፓስተሩም እግዚአብሔርን ሲታዘዝ ነው። ከዚያም እግዚአብሔር በፓስተሩ፡ በቦርዱ፡ በቤተክርስቲያኑ በኩል ይሠራል፡ ሁሉም በአንድ ላይ ሆነው ለእግዚአብሔር መንግሥት አንድ አካል ናቸው። አንድነት ያለው ቡድን ሲኖረን፡ እግዚአብሔር ይሰማል። ምንም ነገር እያስጨንቃችሁ። በምንም ነገር አትደናገጡ።

79 አሁን፡ ይህ እግዚአብሔር ምድርን ለመውሰድ የሾመው ሰው ዓይነት ነው። ሙሴ የተሟላ ሰው ነበር፡ ምንም የማያመቻምች አይነት ሰው ነበር። ክርክሮች እና አለመስማማቶችና፡ የመሳሰሉት፡ ቢኖሩም እሱ አይስማማም። እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው ይህን ነው።

80 ፈርዖን መስማማት ፈለገ፡ እንዲህ አለ፡ "ሙሴ፡ ሁላችሁም መሄድ ትችላላችሁ፡ እና፡ ነገር ግን፡ ልጆቻችሁን ትተዋላችሁ፡ ወይም ከከብቶችህ መካከል የተወሰኑትን እዚህ ትታችሁ መሄድ ትችላላችሁ።"

81 ዲያብሎስ አንድ ክርስቲያን እንዲመጣ የሚፈልገው በዚህ መንገድ ነው። "ቤተ ክርስቲያንን መቀላቀል ምንም ችግር የለውም፡ ነገር ግን ጆንሰንን ይቅር እንዳትለው። ወደ ውስጥ መምጣት ከቻልክ ምንም ችግር አይኖርም… በ… ማጨስ ማቆም የለባችሁም፡ መጠጣታችሁ፣ መዋሸታችሁ፣ መስረቃችሁ፣ ስሕተት መፈለጋችሁ፣ ሰም ማጥፋታችሁን ማቆም አይጠበቅባችሁም። ይህን መተው አያስፈልጋችሁም። ቤተክርስቲያንን መቀላቀል ብቻ ነው የሚያስፈልገው" ይላል።

82 ይሁን እንጂ ሙሴ አላመቻመቸም። ሙሉ በሙሉ ነጻ መውጣት ፈለገ። እንዲህ አለ፡ "አንድም ነገር ወደ ኋላ አንተውም። ጌታን ለማምለክ ስንሄድ፡ ያለንን ሁሉ እንወስዳለን" አለ።

83 ቤተ ክርስቲያን እንዲህ መሆን አለባት። "ጽድቅን እንወስዳለን። ቅድስናን እንወስዳለን። መንፈስ ቅዱስን እንወስዳለን። ወደ መሠዊያው ስንሄድ አንድ የሆነ ቡድን እንወስዳለን። እውነተኛ ቡድን እንሆናለን። ከኋላችን ምንም ነገር አናስቀርም። ሁሉንም እንወስዳለን። እዚህ አንድም ነገር አንተውም።" ታውቃላችሁ፡ ሰዎች ዲያብሎስ እስኪሸነፍ ድረስ እንዲህ ባለ መንገድ መጸለይ ይችላሉ።

84 ሙሴና ቡድኑ ያደረጉት ይህንኑ ነው። ወደዚያ ሄደው በደም ሥር ገቡ። አስተውላችኋል፡ በደም ሥር እስካልገቡ ድረስ፡ ሙሉ ነጻነት አልነበረም። ሙሴ፡ ራሱ፡ ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት ነበረው፡ እስራኤል ግን አልነበረችም። አሁንም ቢሆን ኃጢአት ነበር። ሕዝቡም በሙሴ ላይ አጉረመረሙ፡ እንዲህም አሉ፡ "ለምን እንዲህ ታደርጋለህ? በእኛ ላይ ተጨማሪ ችግር አመጣህ።" ምክንያቱም፡ ፈርዖን የጡብ ቁጥራቸውን በእጥፍ ጨምሯል፡ ወዘተ። ይህ ሙሴ ነበር፥ በሙላት በእግዚአብሔር እጅ ላይ ነበር፡ የእግዚአብሔርን በጐች-ለማስማራት፡ ከበግ መንጋ ፍጹም ነጻ ወጣ። ራሱን፡ ፈጽሞ ነጻ አውጥቷል። ነገር ግን ሕዝቡ ነጻ አልወጣም፡ ምክንያቱም አሁንም በመካከላቸው ማጉረምረም ነበር።

85 አንድ ሌሊት እግዚአብሔር ክርስቶስን የሚወክለው፡ በግ እንዲያርዱ ባዘዘ ጊዜ፡ ደሙም በሂሶጵ ይረጭ ነበር፡ ይህም፡ ተራ ቅጠል (በተለመደ፡ ተራ)፡ በሩ ጉበን ላይና በበሩ መቃን ላይ ተቀባ፡ ያኔ እስራኤል በሙላት ነጻ ወጣ፡ አንዲት ኮቴ እንኳ አላስቀሩም። የእነሱ የሆነው ነገር ሁሉ ነጻ ወጣ። ቤተሰቦቻቸው፡ የሚወዷቸው ሰዎች፡ ሁሉም ነገር በሙላት በደም ሥር ሲሆኑ ነጻ ወጡ።

86 ሁሉም ነገር በደም ሥር በሚሆንበት ጊዜ፡ ቤተክርስቲያን በሙላት ነጻ ትወጣለች። ኃጢአታችሁ በደም ሥር በሚሆንበት ጊዜ፡ ሲጋራ ስታጨሱ፡

ቁማር ስትጫወቱ፡ ማታለላችሁ፡ መሰረቃችሁ፡ መዋሸታችሁ፡ ሁሉም ነገር በደም ሥር በሚሆንበት ጊዜ፡ በሙላት ነጻ ትወጣላችሁ። አንድን ሰው ከበደላችሁት፡ አስተካክሉት። በደም ሥር መምጣት አትችሉም፡ አይቆይም። መምጣት አትችሉም። ይህን እንድታደርጉ የሆነ ነገር አይፈቅድም። ማንነታችሁ በሙላት፡ ፍጹም በደሙ ሥር ሲሆን፡ ፍጹም ነጻ ትወጣላችሁ፣ ከዚያ በኋላ ከዚህ በፊት የማታውቁትን ዓይነት ነጻነት ታገኛላችሁ። ሁሉም ነገር በደም ሥር ሲሆን፡ ለአምላክ መንግሥት ታዛዥ ሆኖ ሲመጣ፡ ከዚያ እውነተኛ ነጻነት ይመጣል።

87 ኢየሱስ በሙላት፡ ፍጹም ሰው ነበር። እንደ ሰው የሚያለቅስ። እንደ ሰው የሚበላ ነበር። እንደ አንድ ሰው ይደክማል። በሥጋዊ አካሉ፡ በሙላት፡ ፍጹም ሰው ነበር። በመንፈሱም፡ በሙላት፡ ፍጹም አምላክ ነበር፡ ስለዚህ ሥጋውን በውስጡ ለነበረው መንፈስ ተገዥ አደረገው። አያችሁ፡ እርሱ እንደ እኛ በሁሉም ነገር ተፈተነ። እርሱ ሰው ነበር እንጂ፡ መልአክ አልነበረም። ሰው ነበር። እርሱ ልክ እንደ እኛ፡ ምኞቶች እና ፈተናዎች ነበሩበት። መጽሐፍ ቅዱስም ይላል። ሰው እንጂ፡ ፈተና የማይደርስበት መልአክ አልነበረም። ዕብራውያን 1፡ እንዲህ ይላል፡ “እርሱ… ” ዕብራውያን 1፡4 እንዲህ ይላል፡ “ከመላእክት ዝቅ እንዲል ተደረገ።” እርሱ ሰው ነበር፡ ሙሉ ሰው ነበር፣ እግዚአብሔር ሙሉ ሰው ወሰደ፡ ፍጹም ነጻነት ለማምጣት፡ በመንፈሱ ሞላው። መንፈስ ቅዱስም ያለ መጠን፡ በውስጡ ነበር። ኢየሱስም እንደ እኛ ተፈተነ። በሙላት አምላክ ነበር። ሙታንን በማስነሳት፡ የተፈጥሮን ማዕበል በማስቆም፡ እንዲሁም ኃይለኛ ነፋሶችን በማስቆም ይህን አረጋግጧል። አምላክ ዛፎችን ሲያነጋግራቸው፡ ታዘዙለት። በውስጡ፡ አምላክ ነበር። ሰውም ሊሆን ይችል ነበር፡ እርሱ ሰው ቢሆንም፡ ራሱን ሙሉ በሙሉ( እንደ ሰው) እግዚአብሔርን ለማገልገል፡ ራሱን በእግዚአብሔር እጅ አሳልፎ ሰጠ።

88 እርሱ ምሳሌያችን ነው። እና ወንዶችና ሴቶች ነን። ደግሞም ክርስቲያኖች ነን። እርሱ ምሳሌያችን ከሆነ፡ ራሳችንን ሙሉ ለሙሉ በመንፈስ ቅዱስ እጅ አሳልፈን እንስጥ፡ ይህም የእግዚአብሔር መንግሥት ተገዥዎች እንድንሆን ነው።

89 ሙሉ በሙሉ ሰው ነበር፣ ሙሉ በሙሉ አምላክ ነበር። ነገር ግን የተፈጥሮ ክፍሎቹን አሳልፎ ሰጠ… የተፈጥሮ አካሉንም አሳልፎ ሰጠ፡ አሳቡ፡ ሰራው ሁሉ፡ ጭንቀቱ አሳልፎ ሰጠና፡ እንዲህ አለ፡ “እኔ አብን የሚያስደስተውን ብቻ እሰራለሁ” አለ። እነሆ አያችሁ። ከሰው ልጆች ፍጹም ነጻ ወጣ። ካህናትና፡ ታላላቆቹም ወደ እርሱ መጥተው፡ እንዲህ አሉ፡ “መምህር ሆይ፡ **እንዲህ-እና-እንዲያ**፡” በሃይማኖታቸውም ሆነ በሃይማኖታዊ ተቋማቸው ሊያስገቡት ሞከሩ። ይሁን እንጂ በእግዚአብሔር ስለታመነ ፍጹም ነጻ ወጣ።

90 ዘማሪው፡ “በእኔ ተማምኗልና፡ አስጥለዋለሁ” አላለምን? አያችሁ? “በእኔ ተማምኗልና፡ ውዴን ከውሾች አድናለሁ።”

91 በሕይወት መጨረሻ ላይ ስንደርስ፡ እኔ ለራሴ እፈልጋለሁ። ለራሳችሁ እንደምትፈልጉ አውቃለሁ። እንዲህ እንድትሉኝ እፈልጋለሁ፡ “በእኔ ስለታመነ፡ ከሞት መንጋጋ አድናለሁ። በትንሣኤው ጠዋት፡ ከመቃብር አወጣዋለሁ፡ በእኔ

ስለታመነ ነፍሱን፡ አካሉንና፡ መንፈሱን፡ ፍጹም ነጻ አወጣለሁ። ምክንያቱም በእኔ ታምኗልና።"

92 የኢየሱስ ሥራዎች ሁሉ የተሟሉ ነበሩ። ሁሉም ነገር በሙላት፡ ፍጹም፡ ነጻ የወጣ ነበር። በለምጽ የተያዘውን ሰው ከለምጽ ፍጹም ነጻ አወጣው። የደም ችግር ያለባትን ሴት፡ ከችግሯ ፍጹም ነጻ አወጣት። በኃጢአት ስርየት ቀን በመሞቱ፡ ዓለምን ከኃጢአት ፍጹም ነጻ አውጥቷል። እያንዳንዱን ኃጢአት ፍጹም ነጻ አውጥቷል። ቤተ ክርስቲያኒቱን ነጻ አወጣ። ስለዚህ እኛ ሰዎች፡ በችግር መኖር አያስፈልገንም። በተሸነፈች ሀገር ውስጥ መኖር አያስፈልገንም፡ ምክንያቱም ዲያብሎስን ድል ነሥቶ አለቆችንና ሥልጣናትን፡ ሁሉ ከእግሩ በታች አስገዝቷል፡ በእናንተም ላይ የመግዛት መብት የላቸውም። እኛ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላን፡ ክርስቲያኖች ነን። ዲያብሎስ እንዲነግረን ማ-... ማድረግ አያስፈልገንም። ክርስቶስ አድኖናል፡ ሙሉ በሙሉ ነጻ አውጥቶናል። ከክፉ ነጻ አውጥቶናል፡ ከኃጢአት ነጻ አውጥቶናል፡ ከልምድ፡ ከንግግር ነጻ አውጥቶናል፡ ከ—ከክፉ አንደበት ነጻ አውጥቶናል፡ ከሁሉም ዓይነት አስጸያፊ ነገሮች ነጻ አውጥቶናል። ፈጽሞ አዳነን በቅዱሱም እጆቹ አኖረን፥ የተሟላ፡ ፍጹም ነጻነት።

93 እርሱ ከሕመማችንን ነጻ አውጥቶናል። እርሱ ከበሽታ ነጻ አውጥቶናል፡ ለዚህም የተሰጠን መብት አለንና። ሃሌ ሉያ! "እርሱ ስለ መተላለፋችን ቆሰሏልና፡ በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን።" እርሱ ፈዋሻችን ነው። ለዚህ ነው ያች ምስኪን፡ ትንሽ፡ ፖሊዮ ያለባት ሴት፡ በካንሰር ሞት-አፋፍ ያለውን ባለቤቷን ለመንከባከብ ስትሞክር፡ ወደ እግዚአብሔር ህልውና ገባች። እምነት ነበራት። ዶ... ዶክተሮቹ ማድረግ የሚችሉትን ሁሉ አድርገዋል፡ ስለዚህ የእግዚአብሔርን መመሪያዎችን ተከተለች እና ሙሉ በሙሉ ነጻ ወጣች።

94 ደቀ መዛሙርቱ ፍጹም ነጻ ወጥተዋል፡ ፍጹም የሆነ ነጻ መውጣት። ለምን? ምክንያቱም እነሱ በሙላትና ፍጹም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተዋል። አንተም፡ የቤተክርስቲያን አባል ብቻ ሆነህ ከፓስተሩ ጋር እጅህን ስትጨባበጥ፡ ወይም... አንዳንድ የመዝለል ልምምድ፡ መጮኽ፡ ወይም በልሳኖች የመናገር፡ ወይም የሌላ ነገር ልምምድ ብቻ ካለህ፥ አሁንም በልብህ ውስጥ ክፋት፡ እንግዳ ድርጊት፡ ውሸት መናገር፡ ሲጋራ ማጨስ፡ ሴቶችን መሻት ካለ፣ ገና ያልተከሰተ ነገር አለ። የሆነ ችግር አለ። "ዓለምንም ሆነ፡ በዓለም ውስጥ ያሉትን ነገሮች የሚወድ፡ በእሱ ውስጥ የእግዚአብሔር ፍቅር የለም።" ተሳስተሃል። "ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ።"

95 ከመንፈስ ቅዱስ ጋር፡ ሁላችንም አንድ መሆን እንፈልጋለን። እያንዳንዱ አባል፡ ከሌላው ጋር አንድ መሆን አለበት። የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ይፈሰሳል። ከክፋት ሁሉ ያነጻናል። ከዓለም ነገሮች ነጻ ወጥተናል። ኢየሱስ፡ "በዚህ ሰዎች ሁሉ፡ ደቀ መዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ፡ ያውቃሉ" ብሏል፡ አንድ አባል ሌላውን አባል በጣም ስለሚወደው ለእሱ ሲል ሊሞት ይችላል።

96 አንድ እኩይ ነገር ሲጀምር፡ ውጫዊው ዓለም፡ አንዳንድ ሴቶች መጥተው እንዲህ ይላሉ፡ "አሁን፡ ተመልከት፡ ውዴ፡ **ይህን፡** ወይም **ያንን** አድርግ፡ **ይህን** ልበስ፡ ወይም **ያንን፡** ወይም **ይህን** አድርግ፡ ከእነዚያ ሆሊ-ሮለሮች ውጣ"

ይላሉ፡ ወይም እንደዚህ የመሳሰሉትን ነገር ይናገራሉ፡ ከእግዚአብሔር ጋር እጅግ አንድ ሆነናል!

97 እንዲህ ትላላችሁ፡ “እንግዲህ፡ ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ ይህ አስከፊ ፈተና ነው።” ክርስቶስ ግን የሞተው ለዚህ ዓላማ ነው። ዲያብሎስ ተሸንፏል። ፍጹም ነጻ መውጣት እንፈልጋለን። የተቀደሰች ንጹሕና ያልተበከለች፡ በበጉ ደም የታጠበች ቤተክርስቲያን እንፈልጋለን። በመንፈስ ቅዱስ በምልክቶች፡ ድንቆችና ተአምራት የተሞላችውን። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ—አርታዒ።] ሁሉንም ሰው ፍጹም ነጻ አውጡ… [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ—አርታዒ።]

98 ውድ አምላክ ሆይ፡ ሙሉ በሙሉ ነጻ ካልወጣ በቀር ምንም ነገር አትወስድም። እንከን ያለበትን መሥዋዕት መቀበል አትችልም። በዚያ ሰው ሕይወት ውስጥ ወደ ኋላ ኃጢአት ካለ፡ ጸሎቱን መቼም ቢሆን አትቀበልም። ይህን ማድረግ አትችልም፡ ጌታ ሆይ። ባለፉት ዘመናት እንዲህ አላደረግህም፡ ዛሬም እንዲህ ማድረግ አትችልም። ነገር ግን መሥዋዕቱ እንከን የለሽ መሆን አለበት። ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፡ እንደተሰዋ ህይወት፡ በመሠዊያው ላይ ራሳችንን ስናቀርብ፡ ጌታ ሆይ፡ እንከን የሚሆንብን ሃጥያት ሁሉ፡ አስወግድልን። ነፍሴን፡ አካሌን፡ ጉልበቴን፡ ጥረቴን፡ ከዚህች ቤተክርስቲያን ጋር፡ ዛሬ ጠዋት በመሠዊያው ላይ አስቀምጣለሁ። በደምህ አንጻን፡ የሠራነውንም ኃጢአት ሁሉ ይቅር በለን። ታላቁ መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ በሀብት ይኑርልን፡ የእርሱ መገኘት ዛሬ ጠዋት ከዚህ ተብርናክል ከእኛ ጋር ይሂድ፡ ይህም በውስጣችን እርሱ ይቅር እንዳለን እናውቃለን። ከዚያም ጸሎታችን፡ “የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን” ይሆናል። ባርከን፡ ጌታ ሆይ።

99 አሁን ከጐናችን ሁን፡ በምሽት አገልግሎት እስክንገናኝ ድረስ ባርከንና ጠብቀን። እንዳትጥለን ዘንድ፡ በንጹሕ እጆችና በንጹሕ ልብ ወደዚህ እንምጣ፡ ጌታ ሆይ፡ ከማንኛውም ነገር በሙላት እና ፍጹም ነጻ መውጣት እንፈልጋለንና፡ ለዓለም ብርሃን እንዳንሆን ከሚያግደን ነገር ሁሉ፥ ተራራ ላይ የተቀመጠ እሳት እንጂ፡ ከዕንቅብ በታች የተቀመጠ አይደለም፡ ነገር ግን ተራራ ላይ የሚቀመጥ እሳት፡ የሰዎችን እግር በትክክለኛው መንገድ ለመምራት ብርሃንን የሚሰጥ ነው። አባታችን ሆይ፡ ስጠን። በኢየሱስ ስምና፡ ለክብሩ እንጠይቃለን። አሜን።

100 ዶክን እጠይቀዋለሁ ከ… ከኋላ ያለ ይመስለኛል፡ ወይም ዲያቆናት መካከል አንዱ ከለ። ቤተክርስቲያኑ ይህንን እንዲያነበው፡ ዶክ፡ ና ይህንን በማስታወቂያ ሰሌዳው ላይ ለጥፍ ቤተክርስቲያኑ ሲወጡ ሊያዩት ይችላሉ። ከዚያም ወንድም ኮሊንስ፡ እ… እሱ እዚህ ከሆነ ወንድም ኮሊንስ ውስጥ ነው? ይህን ሌላኛውን ስጡት።

101 እና፡ እሺ፡ ወዳጄ፡ እና… [ወንድም ብራንሃም ማስታወሻውን ያነባል—አርትዒ።] ቃለ መጠይቅ ማድረግ የሚፈልግ ሰው ካለ። ይህ ሁልጊዜ የተፈቀደ ነው። እኛ ደስተኞች ነን።

ቃለ መጠይቆች አሉኝ። አያችሁ፡ ማድረግ ያለባችሁ ነገር በቅጥራችን መደወል ነው። ቤት ላይ በ—በጣም ብዙ ችግር ነበር፡ ቤተ ክርስቲያን ይህን ታውቃለች። ይህም ስለ እንግዶች ነው። ቤተ ክርስቲያንም ስለዚህ ጉዳይ ታውቃለች። ትንሽ ቊራጭ ወረቀት መቀመጥ አለበት… እዚህም በቤተክርስቲያኑ ውስጥም፡ እንዲቀመጥ አደርጋለሁ፡ ለ-ለሚመጡት። አያችሁ፡

በጣም ብዙ ናቸው፡ ሁሉንም ማዳረስ አንችልም፡ ልክ በቁጥር እንደሚመጡ ነው። አያችሁ? እኛም... በ BUtler 2-1-5-1-9 ብቻ ከደወላችሁ፡ BUtler። [ስልክ ቁጥሩ ተቀይሯል—አርታዒ።] የሚፈልግ ማንኛውም ሰው የሚያይ ማንኛውም አባላት፡ እኔ ሁልጊዜ ሰዎችን በማየቴ ደስተኛ ነኝ። እኛ ግን መደበኛ ሥርዓት አለን። አንዳንድ አስቀድሞ የደወሉ አሉ፡ ብዙ፡ አያችሁ። እንደመጣን፡ አንድ በአንድ፡ እንመጣለን። ከዚያም... መጀመሪያ በነበረው፡ ሁሉምን ነገር ከሰርኡት፡ የወጣ ነበር፡ እንደፈለጉ፡ በመተው፡ ሰዎች ተናደው ወደበታቸው ይመለሱ ነበር። አሁን ሁሉም ነገር በቅደም ተከተል አዘጋጅተዋል። እና አሁን ለመናገር እየሞከርን ያለነው ያ ነው፡ አያችሁ፡ ሁሉንም ነገር በቅደም ተከተል ተሰተካክሏል፡ በትክክል።

እና ይህን ውድ ወገን በ BUtler 2-15-19 (1-5-1-9) ሲደውሉ ማየቴ ደስ ይለኛል፡ ሚስተር መርሲየር ወይም ሚስተር ጎድ፡ እንዳቸው፡ ስልኩን ይመልሱና መቼ ቀጠሮ መያዝ እንደሚትችሉ በትክክል ይነግራችኋል። እዚያ ቦታ አዘጋጅተናል፡ አየር ማቀዝቀዣና፡ ህዝቡን ለመቀበል እና ለእነርሱ ለመጸለይ ተዘጋጅተናል። በማድረጋችን ብቻ ደስተኞች ነን።

102 አሁን፡ ወደ ቤተክርስቲያን የማልመጣበት ምክንያት፡ ሕዝቡ ከሕዝቡ ለመራቅ እየሞከርኩ ነው ብሎ ያሰባል፣ ግን አይደለም። በትክክል በቅደም ተከተል ለ—ለመሆን እየሞከርኩ ነው። አያችሁ? እኔ መሆን የምፈልገው ይህ ነው፡ ሁሉንም ሰው አከብራለሁ። እያንዳንዱ ሰው፡ ማንኛውም ሰው፡ የትም ቦታ፡ በማንኛውም ጊዜ፡ አያችሁ፡ ቀለም፡ ሃይማኖት፡ ከዚህ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። በቀጥታ ወደዚያ እንመጣና ሰዎችን እንገናኛለን። የሚያስፈልጋቸው ነገር ካለ፡ እስኪፈታ ድረስ ከእግዚአብሔር ጋር እንቆያለን። ስለ ሰብሰባዎች ማንኛውንም ነገር ማወቅ ከፈለጉ፡ እንንከባከባቸዋለን እና ፋይል እናደርጋለን። ይህ የመንፈስ ቅዱስ አመራር ብቻ ነው። ያ... ያ መንገድ፡ እኔ እንደማስበው፡ ለሁሉም ሰው በትክክል ተመሳሳይ ነው። ስለዚህ፡ ለሰው ለሌሎች የተለየ አክብሮት የለም፡ አክብሮት የለም።

103 ዛሬ ጠዋት፡ ለመጸለይ የመጡ ህዝቦች አሉ፡ እንግዲያውስ የታመመና እንዲፀልይለት የፈለገ? መልካም። የለም።

ለ... ለዓምልኮ የሚሆን ጥሩ መዝሙር እንዘምር። ዛሬ ጠዋት ምን መዘመር እንችላለን? "ኃጢአቴን ማን ያጥበዋል?" ታውቀዋለህ፡ ቴዲ? "የክርስቶስ ደም ብቻ ነው።" ማን ያጥበዋል...

[አንዲት እኅት ለወንድም ብራንሀም ተናገረች—አርታዒ።] ደህና፡ ወዳጄ። አሁን ለእርሷ መጸለይ ትፈልጋለህ?

በዚህች ሴት ላይ እጄን እጭናለሁ። ለዚህች ሴት እጸልያለሁ። ከእኔ ጋር አንገቶቻችሁን ዝቅ ታደርጋላችሁ፡ ከዚያ፡ ጸጥ በሉ።

104 ውድ አምላክ ሆይ፡ በጣም የታመመች አንዲት ሴት አለች። እኅታችን ካንሰርን ከሌሎች፡ ለመውሰድ እንኳ ሳይቀር፡ ራሷን አሳልፋ ለመስጠት ዝግጁ ሆና፡ አሁን ለራሷ ታማለች። ነገር ግን ከጥቂት ቀናት በፊት፡ ጌታ ሆይ፡ እነዚያ ነገሮች ሲታወቅ፡ ከዚህ ነጻ አውጥተሃል። ራሷን፡ እንድታውቅ ፍቀድላት፡ ከዚያም፡ ጌታ ሆይ፡ ካንተ እንደመጣ ታውቃለች። እጆቼን በላዩኣ ላይ በመጫን፡ ለመችላት ለሌላኛዋ ሴት ምሕረትን እጠይቃለሁ። የእግዚአብሔር

ጸጋ፡ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል... በልባችን ውስጥ ምንም ዓይነት ክፋት ካለ፡ ጌታ ሆይ፡ በመጀመሪያ፡ ለእኛ ግለጥልን፡ ከዚያም እኛ ሄደን፡ ትክክል እናደርጋለን። ከዚያም በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ እንዳለን እናውቃለን፡ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አለን፡ የጠየቅነውን እናገኛለን፡ ምክንያቱም ምንም ዓይነት ጥፋት የለብንም። ጌታ ሆይ፡ ስጠን። በኢየሱስ ስም እጸልያለሁ።

ደህና።

ኃጥያቴን ማን ያጥበዋል?
የክርስቶስ ደም ብቻ ነው፤
ማን ንጹህ ያደርገኛል?
የክርስቶስ ደም ብቻ ነው።

ኦህ፡ ንጹህ ብሩክ ምንጭ
ኃጢአቴን ያጠበው፣
ሌላ ምንጭ አላውቅም፡
የክርስቶስ ደም ብቻ ነው።

105 ኃጢአታችሁ ሁሉ በደም ሥር እንደሆነ የሚሰማችሁ ስንቶች ናችሁ? አሁን እጆችንን ከፍ አድርገን እንዘምር።

ኃጥያቴን ማን ያጥበዋል?
የክርስቶስ ደም ብቻ ነው፣
ማን ንጹህ ያደርገኛል?
የክርስቶስ ደም ብቻ ነው።

አሁን እጆችንን ስናወርድ፡ እጆችንን እንጨባበጥ።

ብሩክ ምንጭ...

በትክክል፡ ዙሪያውን ሁሉ።

... ነጭ እንደ በረዶ፣
ሌላ ምንጭ አላውቅም፡
የክርስቶስ ደም ብቻ ነው።

እሱን ትወደዋለህ? ኣሜን።

አቤት፡ ኢየሱስን ሰወደው፡
አቤት፡ ኢየሱስን ሰወደው፡

አሁን አብራችሁ ሁኑ፡ አሁን። ሁላችሁም እግዚአብሔርን አጥብቃችሁ ያዙ።

ኢየሱስን ሰወደው፡
ቀድሞ ሰለወደደኝ።

በፍጹም አልተውህም...

59-0712 ፍጹም ነጻ መውጣት
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡



VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org